# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 105 ታኅሣሥ 15 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# በመስኖና ቴክኖሎጂ የታገዘ የቡና ልማት

ወርቅነሽ ደምሰው

ዜና ትንታኔ

በአሁኑ ጊዜ የቡና ዋጋ በዓለም ገበያ እየጨመረ ነው። ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት 298 ሺህ ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ አንድ ነጥብ 43 ቢሊዮን ዶላር አግኝታለች። ዘንድሮ ደግሞ መጠኑን ወደ 400 ሺህ ቶን በማሳደግ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማግኘት ታቅዷል። ዘንድሮም ባለፉት አምስት ወራት 117 ሺህ ቶን ቡና ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ ከ178 ሺህ ቶን በላይ በመላክ 797 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንደተገኘ የቡናና ሻይ ባለሥልጣን መረጃ ያሳያል።

በኢትዮጵያ ቡናን በመስኖና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማልማት ምርታማነትን ማሳደግ ቢቻል ተጠቃሚነትን መጨመር እንደሚቻል እየተገለጸ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ በተለያዩ አካባቢዎች ያደረጉትን ጉብኝት አስመልክተው በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው እንዳሉት፤ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ገላን ወረዳ በቀርጫንሼ ትሬዲንግ አማካኝነት በመስኖና ሜካናይዝድ መንገድ ቡና እንዲለማ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በመስኖ እየለማ ያለው የቡና እርሻ በሄክታር 60 ኩንታል ቡና ማግኘት

በመስኖና ቴክኖሎጂ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አገልግሎቱ የውጭ ሀገር ዜጎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት እየጎለበተ መሆኑን ገለጸ

## - የውጭ ሀገር ዜጎችን በሙሉ ለመመዝገብ ዝግጅት እያደረገ ነው

መክሊት ወንደወሰን

አዲስ አበባ፡- እንደሀገር የውጭ ሀገር ዜጎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት (ሲስተም) እየጎለበተ መሆኑን የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አስታውቋል።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የኢሚግሬሽን የውጭ ዜጎች ምዝገባና ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ አዳነ ደበበ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ እስካሁን እንደሌሎች ሀገራት የውጭ ሀገር ዜጎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የተደራጀ ሥርዓት አልነበራትም፡፡

የተደራጀ ሲስተም አለመኖሩ በሕገወጥ መንገድ በሀገሪቱ የሚገኙ የውጭ ሀገር ዜጎች ለመቆጣጠር አላስቻለም፡፡ ለዚህ ችግር መፍትሔ ሊሆን የሚችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ አዲስ ሥርዓት እየጎለበተ ይገኛል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ በሕገ ወጥ መንገድ ገብተው የሚኖሩ ብዙ የውጭ ሀገር ዜጎች መኖራቸውን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ በተለይ በሕገወጥ የወንጀል ድርጊቶች ላይ የተሰማሩ የውጭ ሀገር ዜጎችን ለመቆጣጠር ባለመቻሉ



አቶ አዳነ ደበበ

ብዙ ችግሮች እየተስተዋሉ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሕገወጥ ድርጊቶች ላይ የተሰማሩ ብዙ የውጭ ሀገር ዜጎች አሉ የሚሉት አቶ አዳነ ፤ በሕገ ወጥ መንገድ ገብተው የሚኖሩ ብቻ ሳይሆን ሕጋዊ የሆኑ ብዙ የውጭ ሀገር ዜጎች ሳይቀር ባልተፈቀደላቸው ሥራ ላይ የተሠማሩ መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ በጥቁር ገበያ እና በመሰል የወንጀል ተግባራት የሚሳተፉ ብዙ የውጭ ሀገር ዜጎች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የሱዳን፣ የኤርትራ፣ የሶማሊያ፣ የናይጄሪያ፣ የላይቤሪያ ፣ የጂቡቲ፣ የመን እና የሶሪያ ዜጎች በብዛት ይገኛሉ፡፡ ከላቲን አሜሪካ ሀገራት፣ የሩቅ ምስራቅ ሀገራት ዜጎች በተወሰነ መልኩ እንዳሉም ጠቅሰዋል፡፡

በሕገወጥ ድርጊቶች ላይ የተሰማሩ የውጭ ሀገር ዜጎች በሀገር ኢኮኖሚና ደህንነት ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ ነው የሚሉት አቶ አዳነ፤ የዜጎች የመኖር ህልውና እንዲናጋና በብዙ መልኩ የኢኮኖሚው እንቅፋት እየሆኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እነዚህ ሁሉ ሕገወጥ ዜጎች እንዲኖሩ ያደረገው የሕግ ክፍተት ሳይሆን ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩ እንደሆነ የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ እነዚህ ዜጎች ከመጡበትና ከተፈቀደላቸው ውጭ ሌላ አላማ ሲያራመዱ

አገልግሎቱ የውጭ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









# ተግባራዊነት የራቀው የወል ስምምነት

ልጅዓለም ፍቅሬ

ዜና ትንታኔ

በዓለም በተለያዩ ጊዜያት የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ የተለያዩ ስምምነቶች ቢደረጉም የረባ ለውጥ ሲመጣ አይታይም፡፡ ይባሱንም ዓለምን ከድጡ ወደ ማጡ እያስገባ ይገኛል፡፡ በቅርቡ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀሥላሴ የዘላቂ ልማት እሳቤን ለማዳበር የአየር ንብረት ለውጥ ተግዳሮቶችን ማስቀረት አስቸኳይ ስለመሆኑ ተናግረዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለአየር ንብረት ለውጥ እየተሰጠ ያለው ምላሽ አጥጋቢ ባለመሆኑ አፍሪካውያን አስፈላጊ መፍትሔ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸውም መጠቆማቸው የሚታወስ ነው፡፡

ለዚህም የአፍሪካ ሀገራት ሀብቶቻቸውንና ልማቶቻቸውን ከአየር ንብረት ለውጥ የጸዳ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ያደጉ ሀገራት በየኢንዱስትሪያቸው የሚፈጠረው የአየር ብክለት ተመጣጣኝ ካሳ መክፈል አለባቸው የሚለው ትክክል መሆኑ ብቻ ሳይሆን እነርሱም ያምኑበታል፡፡ ይሁን እንጂ ለመቀነስ ወደ ተግራዊነት ከመግባት ለአንዱ ወገን ማላከካቸው እንዲሁም በየጊዜው የሚገቡት ቃል «ላም አለኝ በሰማይ» አይነት መሆኑ የብዙሃኑ እውነት ነው፡፡

ተግባራዊነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ለአካባቢው አርሶ አደሮች እፎይታን የሰጠው የሰላም ስምምነት

ገጽ 3




# የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በተግዳሮቶች ውስጥም ሆኖ በየዓመቱ ውጤት እያስመዘገበ ነው

**ዳንኤል ዘነበ**



አዲስ አበባ ፡- በኢትዮጵያ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በተለያዩ ተግዳሮቶች ውስጥም ሆኖ በየዓመቱ አበረታች ውጤት እያስመዘገበ እንደሚገኝ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ ።

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጥላሁን ዓባይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት ፣ በኢትዮጵያ ባለፉት አራት ዓመታት አምራች ኢንዱስትሪውን ለማሻሻልና በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማድረግ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ከዚህ ውስጥም የንቅናቄ፣ የሪፎርም ሥራዎች እና የፖሊሲና አሠራር ሥርዓት ማሻሻያዎች መደረጋቸውን ገልጸዋል። በዚህም የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በተለያዩ ተግዳሮቶች ውስጥም ሆኖ በየዓመቱ አበረታች ውጤት እያስመዘገበ እንደሚገኝም አስታውቀዋል።

በዘርፉ ትልቅ ለውጥ የሚያመጡ ውሳኔዎች ከተወሰኑት መካከልም የኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣ የግብርና፣ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ሪፎርሞች እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል፡፡ ለአምራች ዘርፉ አጋዥ የሆኑና ከዲጂታላይዜሽን ጋር የተያያዙ ውሳኔዎች መወሰናቸውንም አንስተዋል።

ለዘርፉ ማነቆ ከሆኑ ችግሮች መካከልም የሎጅስቲክስ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የሰላም ችግርና የግብዓት አቅርቦት ውስንነት እንደሚገኙበት ጠቁመዋል።

ለአምራች ዘርፍ ከፍተኛ ሚና ያለው ከሎጀስቲክ ጋር ተያይዞ ያለው አገልግሎት የላቀ እንዲሆን ተደርጓል ያሉት አቶ ጥላሁን፤ በዘርፉ ያሉትን ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችል የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲጀመር መደረጉን ገልጸዋል። በዚህም ተቋማዊ አቅም እንዲኖረው የሚያስችል በስድስት ክላስተሮች የተደራጁ 35 ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ያቀፈ አደረጃጀት መፈጠሩን አመላክተዋል።

አቶ ጥላሁን ፣ በተለይም አዲሱ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ከዚህ በፊት ለወጪ ምርቶች ብቻ ይደረግ የነበረውን የትኩረት አቅጣጫ በመቀየር ተኪ ምርቶችንም የሚያበረታታ ሆኖ መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

በዚህም በ2016 በጀት ዓመት በተኪ ምርት ሁለት ነጥብ 31 ቢሊዮን ዶላር ለማዳን ታቅዶ ሁለት ነጥብ 844 ቢሊዮን ዶላር በማዳን ውጤታማ አፈጻጸም ማስመዝገብ ተችሏል ብለዋል።

ከዚህ ውስጥ እንደ ዘርፍ ትልቁን ድርሻ አንድ ነጥብ 49 ቢሊዮን ዶላር የያዙት ከምግብና መጠጥ ጋር የተያያዙት ምርቶች መሆናቸውን አውስተዋል፡፡

በኬሚካል 832 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር፤ ማኑፋክቸሪንግና ቴክኖሎጂ 96 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር፤ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች 320 ሚሊዮን ዶላር፤ ጨርቅና አልባሳት 104 ሚሊዮን ዶላር፤ በየደረጃቸው የውጭ ምንዛሬ ማዳን መቻሉን አብራርተዋል።

በሀገሪቱ የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ከሰባት በመቶ ያልበለጠ ድርሻ ያለው መሆኑን ጠቅሰው ፤ የአምራች ኢንዱስትሪው የተሻለ እንዲሆን ለማድረግ በተሠሩ የለውጥ ሥራዎች የዘርፉ ዓመታዊ ዕድገት ወደ 10 ነጥብ አንድ በመቶ ከፍ ማድረግ እንደተቻለም አቶ ጥላሁን ገልጸዋል።

በቀጣይ 10 ዓመታት ይህን ድርሻ ወደ 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ለማሳደግ እቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል ። ከዚህ በተጨማሪም አሁን ያለውን 59 በመቶ የኢንዱስትሪዎች የምርታማነት አቅም ወደ 85 በመቶ የማድረስ እቅድ መያዙንም አመልክተዋል።



ዶክተር መልካሙ አብቴ

# ኢትዮጵያ የኩፍኝ በሽታን በመከላከል ረገድ ስኬት ማስመዝገቧ ተገለጸ

**ሰላማዊት ውቤ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ኩፍኝ እና የኩፍኝ በሽታዎችን በመከላከሉ ረገድ ስኬት ማስመዝገቧን የኢትዮጵያ ጤና ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መልካሙ አብቴ አስታወቁ፡፡

ዶክተር መልካሙ በተለይ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ ካለፉት አሥር ዓመት ወዲህ ውጤታማ የክትባት ዘመቻዎችን ተግብራለች፡፡ ክትትል እና ቁጥጥርን በማጎልበት ለወረርሽኙ ፈጣን ምላሽ መስጠት ተችሏል፡፡ ኩፍኝ እና የኩፍኝ በሽታዎችን የማስወገድ ስትራቴጂ ውጤታማ በሆነ መንገድ በመተግበሯም የኩፍኝ በሽታን በመከላከል ረገድ ስኬት ማስመዝገብ ችላለች፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ ስኬቱ መመዝገብ የቻለው ኢንስቲትዩቱ ካለፉት አስርት ዓመታት ወዲህ ከጤና ሚኒስቴርና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት እንደሀገር ለኩፍኝ ወረርሽኝ በሰጠው ፈጣንና ተከታታይ ስልታዊ ምላሽ ስለመሆኑም አመልክተዋል፡፡

በኢትዮጵያ እኤአ ከነሐሴ 2021 እስከ ታህሳስ 2024 ባለው ጊዜ ውስጥ 78 ሺህ 106 የኩፍኝ በሽታ ተጠቂዎች የነበሩ መሆናቸው ሪፖርቶች ማመላከታቸውን ጠቅሰው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሞቱ መጠንም ዜሮ ነጥብ 81 መድረሱን አስታውሰዋል፡፡

እንደ ዶክተር መልካሙ ገለጻ፤ በኩፍኝ ወረርሽኝ ለተጠቁ እና ከፍተኛ ተጋላጭ ለሆኑ እንደ መቅደላ ያሉ አካባቢዎች ትኩረት በመስጠት ተከታታይነት ያላቸው በርካታ ቅንጅታዊ የክትባት ዘመቻዎች ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ ወረርሽኙን በመከላከልና በመቆጣጠር እንዲሁም በማስወገድ ሥራ ሂደት በከፍተኛ ደረጃ ለዘመቻው የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ እጥረት ገጥሟቸው እንደነበር ተናግረዋል፡፡

የኩፍኝ ወረርሽኝን ለመከላከል ረገድ ትልቅ እንቅፋት ከሆኑት መካከል አንዱ የኩፍኝ መከላከያ ክትባት ግብዓት መሆኑን ጠቁመው፤ ችግሩ የሚፈታበት አማራጭ መንገድ እየፈለጉ በመሄድ በኢትዮጵያ እኤአ ከነሐሴ 2024 ጀምሮ የኩፍኝ በሽታ ወረርሽኝ እና ገዳይነት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ማድረግ መቻሉ መረጋገጡን አብራርተዋል፡፡

ለአብነትም ኢትዮጵያ የኩፍኝ እና እንደትኩሳት ያሉ ኩፍኝ ያልሆኑ በሽታዎች (NMFR) ከአራት ነጥብ ዜሮ በመቶ ወደ ሁለት ነጥብ አራት በመቶ ዝቅ ማድረጓን አስታውቀዋል፡፡

እርሳቸው እንደተናገሩት፤ ኩፍኝ በከፍተኛ መጠን የሚተላለፍ በሽታ ሲሆን፣ ትኩሳት፣ ሽፍታ፣ ሳል፣ የዓይን መቅላት እና እንባን የሚያስከትል ከባድ በሽታ ነው። በዋነኛነት የሚተላለፈው ኩፍኝ የያዘው ሰው ሲያስል ወይም ሲያስነጥስ በአየር አማካኝነት ወደ ሌላው ሰው የሚዛመት መሆኑን ገልጸዋል።



# “ምክር ቤቱ የንግዱን ማህበረሰብ የሚመጥን ቁመና ላይ አይደለም”

**- የዳይሬክተሮች ቦርድ**

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ማህበረሰብ የሚመጥን ቁመና ላይ አይደለም ሲል የምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ገለጸ።

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ፣ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ አስመልክተው በሰጡት መግለጫ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀረበውን ውሳኔ መቀበላቸውን ገልጸው፣ በምክር ቤቱ የተስተዋለው የውጭ ጉዞና የተጋነነ ምንዛሬ መኖሩ አንዱ ችግር ነው ማለቱ ትክክል ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የንግዱን ማህበረሰብ ሀብት በማባከኑ፤ የተጋነነ የውጭ ምንዛሬ የስተዋለበት፤ ትላልቅ የግዢ ፖሊሲዎች ጥሰት የተፈጸመ መሆኑ የንግዱን ማህበረሰብ የማይመጥን አድርጎታል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ቦርዱ ያላወቀው አዳዲስ ቅጥር፤ የውስጥ እድገት አሠራርና የትልልቅ ግዢ የፖሊሲ ጥሰት መፈፀሙን፤ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በምክር ቤቱ መኖራቸውን ቦርዱ መግለጹ ተገቢ መሆኑንም በመግለጫቸው ጠቁመዋል።

የዳይሬክተሮች ቦርድ ለበርካታ ወራቶች ባደረጉት ውይይትና ግምገማ ምክር ቤቱ የንግዱን ማህበረሰብ የሚመጥን ቁመና ላይ አመለሆኑን አረጋግጠናል ብለዋል በመግለጫቸው።

የምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነሐሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ የፖሊሲ፣ የሕግና የአሠራር ጥሰት በፈጸሙ ኃላፊዎች አስተዳደራዊ ርምጃ የመውሰድና ክስ ለመመስረት ዝግጅት እያደረገ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ቦርዱ የምክር ቤቱን አፈፃጸም ገምግሞ የንግዱን ማህበረሰብ የሚመጥን ምክር ቤት ለማድረግ የሪፎርም ሥራዎች እንዲደረግ ውሳኔ ማሳለፉንና ምክር ቤቱም ለውጡን ተግባራዊ ለማድረግ እየሠራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

የምክር ቤቱን የቀደመ ሥራና ቁመና ለመመለስ በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝም ገልጿል።

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እያካሄደ የሚገኘው ስር ነቀል ለውጥም የንግዱን ማህበረሰብ የሚመጥን፤ የሚያበረታታ፣ ኢንቨስትመንትን የሚስብ፣ የተጣሱ ደንቦችን የሚያስከብር እና የፖሊሲ ክፍተቶችን የሚያሻሽል ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የትልልቅ የግዢ ፖሊሲዎች ጥሰትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ተስተውለዋል በሚል በ23 ጥቆማዎች ሳቢያ የኦዲት ኮሚቴ ከቦርድ አባላት ተዋቅሮ ምርምር እንዲካሄድ መወሰኑ የሚታወቅ መሆኑን አውስተዋል፡፡

# ለአካባቢው አርሶ አደሮች እፎይታን የሰጠው የሰላም ስምምነት

**መዓዛ ማሞ**

**ዜና ሀተታ**

ወይዘሮ አየለች በቀለ ይባላሉ፡፡ ነዋሪነታቸው በወለጋ ሆሮጉዱሩ ዞን ነው። የሚኖሩበት አካባቢ እጅግ በጣም ለምለምና ለግብርና ልማት ምቹ መሆኑን የሚናገሩት ወይዘሮ አየለች፤ በአካባቢያቸው ሰላም ባለመኖሩ ምክንያት አርሶና ምርትን አምርቶ ለገበያ ለማቅረብ ይቅርና ወጥቶ መግባት ፈታኝ ነበር ፡፡ ይህም እንደምንም ለራስ ከመሆን ባለፈ ለሌሎች መትረፍ ሳይቻል ቆይቷል ይላሉ።

በአካባቢው በነበረው ግጭት ምክንያት ሰዎች ወጥተው መግባት፣ አርሶ ማምረት ፈተና ሆኖ መቆየቱን የሚናገሩት ወይዘሮዋ፤ ወጥቶ የመቅረት ክስተቶችም እንደሚያጋጥሙ አውስተዋል፡፡

"ዛሬ ምን ይፈጠር ይሆን?" በሚል ስጋት ውስጥ ከወደቅን ዓመታት ተቆጥረዋል የሚሉት ወይዘሮ አየለች፤ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ከኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ጋር ያደረገው የሰላም ስምምነት ለአካባቢው ነዋሪዎች የሰላም እፎይታን የሚሰጥ መሆኑን ተናግረዋል።


አካባቢያቸው አርሰው ምርታማ የሚሆኑበት፣ አርብተው ጥሩ ውጤት የሚያገኙበት ለምለም ምድር ነው የሚሉት ወይዘሮዋ፤ የተደረገው የሰላም ስምምነት ሰላምን የሚያጸና ከሆነ በስፋት በማልማት ምርቱን ወደ ለሌሎች አካባቢዎች ጭምር ለገበያ ማቅረብ ይቻላል ነው ያሉት።

የተደረገው የሰላም ስምምነት ሰላምን በማምጣት እና ለአርሶ አደሩ እፎይታን በመስጠት ትልቅ ፋይዳ እንዳለው የሚናገሩት ወይዘሮ አየለች፤ የክልሉ መንግሥት የተደረገው የሰላም ስምምነት እንዲጸና ቀበሌ ድረስ በመውረድ መሥራት አለበት ይላሉ።


አቶ ሃይሉ ቀንዓ ደግሞ የቄለም ወለጋ ዞን ወቀቤ ወረዳ ነዋሪ ናቸው። እሳቸውም በአካባቢያቸው ሰላም ከጠፋ ዓመታት ተቆጥረዋል ።ይህን ተከትሎም በርካቶች "የመንግሥት ደጋፊ" ናችሁ በማለት ከገንዘብ ክፊሉ ጀምሮ የተለያዩ ቅጣቶች ሲደርስባቸው እንደነበርም ይናገራሉ።



ወይዘሮ አየለች በቀለ



አቶ ሃይሉ ቀንዓ



አቶ በቀለ አራርሶ

ነዋሪው ከመፈናቀል ጀምሮ የተለያዩ ችግሮች ሲደርስበት እንደነበረ የሚናገሩት አቶ ሃይሉ ፤ በግጭቱ ምክንያት የመንገድ መዘጋትና የመብራት አገልግሎት መቆራረጥ ያጋጥም ነበር፡፡ እንዲሁም የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ሳይቻል መቅረታቸውንም ያወሳሉ።

ሰላም ከመጣ ምርታማ የሆነው ቄለም ወለጋ ምርቶችን ወደ ሌሎች አካባቢዎች በመላክ በጋራ ተረዳድቶ መኖር እንደሚያስችልም ይናገራሉ። ልጆች በሰላም ወጥተው የሚገቡበት እና ስጋት የሌለው ኑሮ ለመኖርም ሰላም መፈጠር ትልቅ ፋይዳ አለው ይላሉ።

የወለጋ ሆሮጉድሩ አቤ ደንጎሩ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት ደግሞ አቶ በቀለ አራርሶ በአካባቢያቸው በነበሩ ግጭቶች ሰላማዊ ሰዎች ይገደሉና መሠረተ ልማቶችም የከፋ ጉዳት ያጋጥማቸው እንደነበር ያስታውሳሉ ። በዚህ ምክንያት ህብረተሰቡ መንገድ እና መብራት ጭምር በማጣት ከፍተኛ ችግር እንደሚገጥመውም ይናገራሉ።

አሁን ላይ የክልሉ መንግሥት ከኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ጋር ያደረገው የሰላም ስምምነት ለህብረተሰቡ እፎይታን የሚፈጥር መሆኑንም ይናገራሉ። በአካባቢው የሰላም አለመኖር ችግር ዋነኛ ተጎጂው አርሶ አደሩ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ በቀለ፤ ሰላም መፈጠሩ ለአርሶ አደሩ እረፍት በመስጠት እንዲሁም የተቋረጡ መሠረተ ልማቶች እንዲቀጥሉ በማድረግ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ነው የገለጹት።

# ሁለንተናዊ ዝግጅት የሚሻው ጋብቻ

**ቤዛ እሸቱ**

**ዜና ሀተታ**

በኢትዮጵያ ጋብቻ ከወሳኝ ኩነት በተጨማሪ፣ በሃይማኖትና በባህል ስለሚፈጸም ትክክለኛውን የተጋቢዎች ቁጥር ማግኘት አደጋች እንደሆነ ይገለጻል። የአዲስ አበባ የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያሳየው በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የተመዘገበ ጋብቻ በ2016 ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ከተፈጸመ ጋብቻ ጋር ሲነጻጸር የ15 በመቶ ብልጫ አለው፡፡ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የተፈጸመ የፍቺ ምዝገባ በ2016 በጀት ዓመት ከተመዘገበው የ53 በመቶ ብልጫ እንዳለው ያመለክታል፡፡ ይህ ብቻ ፍቺ ጨምሯል የሚለውን ለመወሰን በቂ ባይሆንም የሀገር መሠረት የሆነው ጋብቻ ዘላቂ እንዲሆን ግን ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንዳለበት አመላካች ነው፡፡

የሥነ-ልቦና ባለሙያ አቶ ሽመልስ ገበየሁ ጋብቻ ትልቅና ሰፊ የሕይወት ሽግግር ነው፡፡ ሰዎች ወደ ጋብቻ ከመግባታቸው በፊት ለጋብቻ ዝግጁ ነኝ ወይ? የሚለውን መመለስ አለባቸው ይላል፡፡ ዝግጁነቱ ከአካላዊ ዝግጁነት አንስቶ እድሜዬ ለጋብቻ ደርሷል ወይ? የሚለውን መወሰን አለባቸው፡፡

አንዳንድ ጊዜ እድሜያቸው ለጋብቻ ቢደርስም ጋብቻ ሲባል የፍርሃት፣ የድንጋጤ፣ ኃላፊነት መሸከም አልችል ይሆን ብሎ የመጠራጠርና ጋብቻን ተከትሎ የሚመጡ ነገሮችን የመፍራት ሁኔታ እንደሚታይ ጠቁሟል። ለዚህም ትዳር ስሜታዊ ዝግጅት ይፈልጋል ነው ያለው።

ትዳር በቂ ዝግጅት ይፈልጋል የሚሉት የሥነ-ልቦና ባለሙያው፤ ጥንዶች ለሰርጉ ድግስ ከሚደረገው ዝግጅት ቀንሰው ሕይወታችንን እንዴት እንምራው? ላይ ሲያውሉት እንደማይታይ ይናገራሉ፡፡ ከአዳራሽ መረጣና ከአገባብ አንስቶ እስከ ፎቶ አነሳስ ረዥም ጊዜ ወስደው እንደሚዘጋጁት ሁሉ የጋብቻ ሥልጠና ወይም ልምድ ልውውጦችን እንደአንድ የዝግጅታቸው አካል ሊያደርጉ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡




የቅድመ ጋብቻ ሥልጠናዎች በሥነ-ልቦና ባለሙያዎች የሚሰጡ ድርጅቶች ጋር ወይም በእምነት ተቋማት ማግኘት ይችላሉ፡፡ ሥልጠናውን ለመጋባት ያሰቡ ጥንዶች የዝግጅታቸው አካል ሊያደርጉት ይገባል ነው ያሉት፡፡

እንደ ሥነ-ልቦና ባለሙያው ማብራሪያ፤ አንድ ሰው ወደ ጋብቻ ሲገባ እኔ ጥሩ ባል ወይም ሚስት መሆን እችላለሁ ብቻ ሳይሆን ጥሩ እናትና ጥሩ አባት መሆን እችላለሁ ወይ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያሻል። ትዳር ከመመሥረቱ በፊት ለጋብቻና ተያይዘው ለሚመጡት ነገሮች የአእምሮ ዝግጁነትና ብስለት ያስፈልጋል። ጥንዶቹ ኑሮን ሲመሩ በኢኮኖሚ ደረጃ ዝግጁ መሆናቸውን ማየት ይገባል፡፡ ለዚህም ከቤተሰብ ጋር ምን አይነት ግንኙነት ይኖረኛል? ችግር ቢያጋጥም እንዴት እፈታለሁና? መሰል ነገሮች በቅድመ ጋብቻ ዝግጅት ውስጥ መታየት ያለባቸው ናቸው፡፡

ጠበቃና የሕግ አማካሪ ብሩክ አያሌው ማሞ፤ በቤተሰብ ሕጉ በሀገራችን ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች መደንገጋቸውን ያስረዳሉ። ጋብቻው በሁለቱም ፈቃደኝነት ላይ ሊመሠረት ይገባል።ጥንዶቹ እድሜያቸው 18ና ከዛ በላይ መሆን አለበት።፡ የቅርብ የሥጋ ዝምድና ሊኖር አይገባም፡፡ ምንም እንኳን የስጋ ዝምድና ባይኖርም እንደ ልጅ ካሳደጉትና ማህበረሰቡም እንደልጅ እውቅና ከሰጠው ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸምና በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንደማይቻል ያስረዳሉ፡፡

እንደሕግ ባለሙያው ማብራሪያ ጥንዶች ጋብቻን ሲያስቡ የራሳቸውንም ሆነ የጥንዳቸውን እድሜ፣ ፍቃደኝነት፣ የጋብቻ ሁኔታና ዝምድና ሊያውቁ ይገባል፡፡ ሕጉ ተጋቢዎች ከጋብቻ በፊት ያፈሩት ንብረት የግላቸው ሆኖ እንዲቀር መብት ይሰጣል፡፡ ይህ እንዲሆን መጀመሪያ በጋብቻ ውል መታሰር አለበት፡፡ በውሉ ላይ ንብረቱ ተዘርዝሮ በባለቤቱ ስም ይቀመጣል፡፡ ከጋብቻ በኋላ የሚፈራ ንብረት የጋራ ይሆናል፡፡ ጋብቻው ባይቀጥልና ቢፈርስ የንብረት ክፍፍል ላይ ንብረታቸውን መውሰድ ይችላሉ፡፡

የጋብቻ ውል ማሰር የሚፈልጉ ጥንዶች ከመጋባታቸው አስቀድሞ የጋብቻ ውል ማሰር ይችላሉ፡፡ የጋብቻ ውል ሲባል ብዙ ሰዎች ንብረትን ብቻ ታሳቢ ያደርጋሉ የሚሉት አቶ ብሩክ፤ ውሉ ግላዊ ግንኙነቶችንም ማካተት ይችላል ብለዋል፡፡ በውሉ ላይ ልጅን በተመለከተ ምን እንደሚያደርጉ፤ ገቢንና ቤትን ማን እንደሚያስተዳድር በግል ቤት ውስጥ የሚወሰኑ ነገሮችን በውሉ ማካተት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

እንደ የሕግ ባለሙያው ማብራሪያ፤ የጋብቻ ውል ሳያስሩ ጋብቻ የፈጸሙ ጥንዶች በፍቺ ወይም አንዱ ወገን በሞት በሚለይበት ወቅት ለረዥም ክርክርና ወጪ ይዳርጋሉ፡፡ አንድ ሰው ከጋብቻ በፊት ያፈራው ንብረት እንደሆነ በበቂ ማስረጃ ማረጋገጥ እስካልቻለና የጋብቻ ውል ከሌላቸው ምንም እንኳን ከትዳር በፊት የፈራ ንብረት ቢሆን፤ ንብረቱ የጋራ እንደሆነ ተቆጥሮ እንዲካፈሉ ሊፈረድበት እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

አቶ ሽመልስ ጥንዶች በእጮኝነት ጊዜ ፍቅርንም ጸብንም አስተናግደው ወደ ጋብቻ ቢገቡ ይመከራል ይላሉ፡፡ በተለይ አንዳንድ ጥንዶች ተጣልተን አናውቅም፤ ተጨቃጭቀን አናውቅም፤ ሲሉ እንደሚያፍሩ ይገልጻሉ፡፡ ትዳር ውስጥ ገብተው ከሚማሩት በእጮኝነት ጊዜያቸው የሃሳብ ልዩነት ሲኖር እንዴት እናስተናግደዋለን የሚለውን አስቀድሞ ማየታቸው ትልቅ ጥቅም አለው ፡፡ ምክንያቱም ሲገቡበት እንግዳ አይሆንባቸውም ነው ያሉት፡፡

የቅድመ ጋብቻን ሥልጠናን የሚወስዱ ጥንዶች ልዩነቶች ሲያጋጥሙ መታረቅ የሚችለውን አስታርቀው መታረቅ የማይችለውን ልዩነታቸውን ተቀብለው ለመኖር ወስነው ስለሚገቡ የመፋታት ዕድላቸው አነስተኛ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የሥነ-ልቦና ባለሙያው ከዚህ ቀደም እናቶች በቡና ዙሪያ ችግሮቻቸውን ይወያዩ ነበር፤ ወንዶቹም ሰብሰብ ብለው የሚተነፍሱበት አማራጭ ነበራቸው፡፡ መደበኛ በሥነ-ልቦና ባለሙያ የተደገፈ መደበኛ የምክክር ክፍለጊዜ ባይኖርም ከልምድ አንዳቸው ለሌላቸው መፍትሄ እያመላከቱና ከጋብቻ በፊትም እየተጠናኑ የሚቆዩበት ጠንከር ያለ ማህበራዊ ግንኙነቶች እንነበር አንስተዋል፡፡ በሃይማኖት አባቶች፣ በሀገር ሽማግሌዎችና እርስ በእርስ ልምድ ልውውጡም የፍች መጠኑ ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረጉን ገልጸው፤ አሁን እነዚህ ግንኙነቶች ላልተዋል ነው ያሉት፡፡

በአሁኑ ጊዜ ዘመኑ ከቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ ጥንዶች የሚያጋጥሟቸው ፈተናዎች ከበፊቱ እንደሚለይ ጠቁመዋል፡፡ ሰዎች በቀላሉ ስለፍቅር ግንኙነትም ሆነ ስለሌላው ነገር በእጅ ስልካቸው በርካታ አስፈላጊም፤ አላስፈላጊም መረጃ የሚያገኙበት ዘመን ነው የሚሉት አቶ ሽመልስ፤ በዚህ ዘመን ያሉትን ፈተናዎች ያለ እውቀት ልንፈታቸው አንችልም ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ሰዎች የቅድመ ጋብቻ ሥልጠና መውሰዳቸው የሚገቡበትን የትዳር ሕይወት አውቀውትና ለዛም ዝግጁ ሆነው እንዲገቡ እንደሚያግዛቸው አስረድተዋል፡፡

# በመስኖና ቴክኖሎጂ የታገዘ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚያስችል ነው፡፡ ይህን ተሞክሮ ወደ ሁሉም ቡና አምራች አካባቢዎች በማስፋት የዘርፉን የወጪ ንግድ ገቢ ማሳደግ እንደሚገባም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ ማስገንዘባቸው ይታወቃል፡፡

የቡና ምርታማነት ወደ ቡና አምራች አካባቢዎች ለማስፋት ምን ማድረግ ይጠበቃል? በጉዳዩ ላይ ያነጋገርናቸው በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ቡና ላይ ለረጅም ጊዜ ምርምር ያደረጉት ፕሮፌሰር ዋሱ መሀመድ አሊ በኢትዮጵያ በሄክታር ከ45 እስከ 50 ኩንታል ቡና የማምረት አቅም እንዳለ ጠቅሰው፣ በተያዘው ቴክኖሎጂና መስኖ ልማት ምርታማነቱን በሄክታር 60 ኩንታል ለማድረስ መታሰቡ ሊያስኬድ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡

በተለምዶ የሚሠራበት ቡናን ዛፍ ውስጥ ማልማት /በሼድ/ አነስተኛ ምርት እየሰጠ እስከ 40 እና 50 ዓመት ቡና ምርት ሲለቀም የነበረበት ሁኔታ መኖሩን ይገልጻሉ። ይህን ቴክኖሎጂ በደንብ ማስፋት ከተቻለ በሄክታር 60 ኩንታል ብቻ ሳይሆን ከዚያ በላይ ማምረት ይቻላል ባይም ናቸው፡፡

እንደ ብራዚልና ቬትናም ያሉ ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየው በሚጠቀሙበት የግብርና ቴክኖሎጂ ልክ አሁን ላሉበት ደረጃ መድረሳቸውን ነው ሲሉ ገልጸው፤ እንደ ሀገር ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቡና ምርታማነት በዚህ ልክ ማስፋፋት እንደሚቻል ያመላክታሉ፡፡

ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት፤ ለአብነት ብራዚሎች በጠባብ ቦታ አድርገው ለማሽኑ ብቻ መንገድ ትተው በማሽን ያመርታሉ፡፡ በብዛት የሚያመርቱበት አንድና አንዱ ምክንያትም ይሄው ነው፡፡ ‹‹በዚህም ከእኛ የተሻለ ያመርታሉ፡፡ ከእኛ በኋላ በቅርብ የጀመሩ 40 ዓመት ያልሞላቸው ቬትናሞችም እንዲሁ ቡና በብዛት እያመርቱ ነው›› ብለዋል፡፡

አርሶ አደሩ በቴክኖሎጂው ተጠቅሞ ቡና ወደ ማልማት ሲገባ በበቂ ባለሙያዎች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሁም ክትትል ሊደረግለት እንደሚገባም ይጠቁማሉ። ጅምሩ ጥሩና ለሌሎችም ምሳሌ እንደሚሆን አመልክተው፣ አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባም አስገንዝበዋል። በመንግሥትም፣ በምርምር ረገድም መደገፍ ከተቻለ ማስፋቱ ችግር አይሆንም ይላሉ፡፡

‹‹እኛ እጃችን ላይ ያለውን ወርቅ ሳንጠቀምበት ኖረናል፡፡ ኬንያ በሄክታር ከ30 እስከ 40 ኩንታል ታመርታለች፤ ቁጭት የሚኖረው ካለ እና በመንግሥት በኩል የባለሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ካለ ይህንን ለማድረግ የተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው የሚፈጀው ›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡



ቡና ብዙ ምርታማ ለመሆን ከአራት ዓመት ጊዜ በላይ የሚፈጅ መሆኑን ፕሮፌሰር ዋሱ ጠቅሰው፣ አርሶ አደሩም ቢሆን አንድ ጊዜ ተጠቅሞ ካየ በራሱ ያስፋፋዋል ይላሉ። ብልጭ አድርጎ ከመተው ሥር ይዞ በደንብ እንዲሰፋ ማድረግ ላይ ሊሠራ እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

ፕሮፌሰሩ ስጋታቸውንም ጠቁመዋል፤ በማስፋቱ ሥራ በርካታ ችግሮች ሊገጥሙ እንደሚችሉ ገልጸው፣ የመጀመሪያው ችግር ከፍተኛ የባለሙያ እጥረት ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በቡና ዘርፍ ላይ ብቻ የሰለጠነ ባለሙያ የለም፡፡ እንደ ብራዚል ያሉ ሀገራትን ተሞክሮ ስንመለከት የቡና ባለሙያዎች (ከዲግሪ ጀምሮ እስከ ፒኤች ዲ ድረስ) የሚያሠለጥኑበት ራሱን የቻለ ኢንስቲትዩት አላቸው፡፡ በእኛ ሀገር በዲግሪ ደረጃ በቡና ብቻ የሠለጠነ አርሶ አደሩን ሊደግፍ የሚችል ባለሙያ የለንም፡፡ በቴክኒክም ሆነ በእውቀት ከአርሶ አደሩ የተሻለ ባለሙያ ሊኖር ይገባል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

ሁለተኛው ሊያጋጥም የሚችለው ችግር ለማምረቱ ሥራ የሚውል ግብዓት በጊዜውና በበቂ ሁኔታ አለማቅረብ መሆኑን ጠቁመው፣ የቡና ተክል መግረዣ ፣ መጎንደያ፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያና የመሳሰሉትን በወቅቱ ማቅረብ ያስፈልጋል ነው ያሉት፡፡

ከዘርፉ የሚወጣው ገንዘብ ይህን ሥራ መልሶ መሥራት እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ አቅሙ ስላለ ከወጪ ጋር ተያይዞ መንግሥትን ችግር ውስጥ የሚከት ነገር አይኖርም ይላሉ፡፡ ምርታማነቱ ላይ በመሥራት የተሻለ ምርት ማግኘት እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ምርታማነት የሚያሳድግና ምርምር ሥራውን የሚሠራ የተጠናከረ መሥሪያ ቤት ያስፈልጋል፡፡ እንደ ብራዚሎቹ የጅማን ምርምር ማዕከል ኢንስቲትዩት አድርጎ ባለሙያዎች በማሠልጠን በቡና ማምረት ላይ ተመሥረተው ብቻ ኑሮአቸውን የሚመሩ አርሶ አደሮች በበቂ ባለሙያዎች እንዲረዱ ሊደረግ ይገባል። የቡናና ሻይ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤትንም ማጠናከር ይገባል፡፡

ሥራው በዘርፉ የተሰማሩ ነጋዴዎችን፣ ዩኒየኖችን፣ ላኪዎችን፣ ወዘተ በማናቀናጀት መሥራትን እንደሚጠይቅ ገልጸው፤ ትኩረት ሠጥቶ በመሥራት ከተቻለ ሥራውን ባለሙያው የሚሠራው ዘርፍ ራሱን በራሱ መደገፍ የሚችል ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡና ማህበር ፕሬዚዳንት ሁሴን አምቦ (ዶ/ር)፤ የፕሮፌሰሩን ሃሳብ የሚያጠናክር ሃሳብ አላቸው፡፡ ቴክኖሎጂው የሚበረታታ ነው ይላሉ፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ቴክኖሎጂው ለአርሶ አደሩ በሁለት መልኩ ይጠቅማል፣ አንደኛው ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ሁለተኛው ጥራቱን የጠበቀ ቡና ማምረት ማስቻል ናቸው፡፡

ቴክኖሎጂውን ለማስፋት ግን ጊዜ እንደሚፈልግ ተናግረው፣ አሁን ባለው የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች አቅም ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑ በቅድሚያ በደንብ መታየት እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል፡፡

ሁሴን (ዶ/ር) እንዳስታወቁት፤ ቡና በመካናይዜሽን በመጠቀም በሄክታር 60 ኩንታል ለማምረት ሰፊ መሬትና ቦታ ይፈልጋል፡፡ ይህን መጠቀም የሚችሉት አቅም ያላቸው አርሶ አደሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አነስተኛ ማሳ ባላቸው አርሶ አደሮች ይዞታ ላይ ይህን መተግበር እንደሚያዳግትም ያመላክታሉ፡፡

እንደ ቀርጫሼ እና ሆራይዘን ያሉት ድርጅቶች ሰፊ ቦታ እንዳላቸው ፕሬዚዳንቱ ጠቅሰው፣ እነዚህ ድርጅቶች ቴክኖሎጂ ተጠቅመው በመስኖ ማምረት ይችላሉ፤ አነስተኛ ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮች ግን ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ይቸገራሉ ብለዋል፡፡

ቡና ለውጭ ገበያ እየቀረበ ያለው ከአምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን አርሶ አደሮች ተሰብስቦ መሆኑን ጠቅሰው፣ የዚህ ቡና እርሻ በተበታተነ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ያመላክታሉ፡፡ ቴክኖሎጂውን ለማስፋት መሬት አሲይዞ መሥራት እንደሚጠይቅ ጠቁመው፤ ለዚህም እቅድ፣ እውቀትና ቴክኖሎጂ ይፈልጋል ነው ያሉት፡፡

እሳቸው እንደተናገሩት፤ እንደ ሀገር ያለን እርሻ የተበጣጠሰ በመሆኑ ለመካናይዜሽን አይመችም። እርሻው በሰፊ ማሳ ላይ እየተካሄደ አይደለም፤ ይህም ቴክኖሎጂ ለማስፋት ተግዳሮት ይሆናል፡፡ ቴክኖሎጂውን ለማስፋት ከችግኝ ጀምሮ የመሬት ዝግጅት እና የመሳሰሉት አስፈላጊ ሥራዎች ታቅደው በደንብ መሠራት አለባቸው፡፡

ያለውን እውቀትና ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ የቡና መሬት ወደዚህ ቴክኖሎጂ እንዲመጣና በመስኖ እንዲለማ በማድረግ የቡናን ምርታማነት ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ሁሴን (ዶ/ር) ጠቁመዋል፡፡ በየቦታው መስኖን መጠቀም ከተቻለ በዓመት ሁለት ጊዜ ማምረት እንደሚቻልና በዚህም የቡና ምርታማነትን ይበልጥ ማሳደግ እንደሚቻል አመልክተዋል፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ኢትዮጵያ የቡና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እየሠራች መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን ተከትሎም ዓመታዊ ቡና የማምረት አቅም አንድ ሚሊዮን ቶን ደርሷል፡፡

ኢትዮጵያ በቡና ምርት ከብራዚልና ቬትናም ቀጥላ ሶስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህን ደረጃዋን ለማሳደግ በመሥራት ላይ ናት፡፡ ሀገሪቱ በርካታ ሀገራት እያለፈች አሁን ላለችበት ደረጃ የደረሰች ሲሆን፣ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት የጀመረችውን ያረጁ የቡና ተክሎች ጉንደላና ችግኝ ተከላ አጠናክራ በመቀጠል ከቡና የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ በእጅጉ ለማሳደግና ተጠቃሚ ለመሆን በትኩረት መሥራት ይጠይቃል።

# ተግባራዊነት የራቀው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ባሳለፍነው ህዳር ወርም 29ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ(ኮፕ29) በአዘርባጃን ባኩ ከተማ ተካሂዷል፡፡ በጉባዔው የአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ በታዳጊ ሀገራት ላይ የሚያስከትለውን ጫና መቋቋሚያ 300 ቢሊዮን ዶላር ቢመደብም በርካቶች ውሳኔውን ተቋውመውታል፡፡ ከዚህ ቀደም ይሰጥ ከነበረው 100 ቢሊዮን ዶላር ማሳካት ሳይቻል አሁን ደግሞ ሌላ የማይጨበጥ ተስፋ በሚል እንደሆነ ተገልጿል፡፡

የበለጸጉ ሀገራት በሚፈጥሩት የአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ ዳፋውን የሚቀበሉት ታዳጊ ሀገራት ሁኔታውን ለመቋቋም ቢያንስ አንድ ነጥብ 3 ትሪሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልግ የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የምድር እጣ ፈንታ በሚቀጥሉት አምስትና 10 ዓመታት በኮፕ29 ጉባዔና በሀገር ደረጃ በሚወሰድ ርምጃ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ለአካባቢ ብክለት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያበረክቱ ሀገራት ከራስ ወዳድነት እሳቤ መውጣት እንዳለባቸውና የአየር ንብረት ለውጥ መቀነስ ብሎም የተረጋጋች ዓለም ለመፍጠር ተግባር ተኮር እንቅስቃሴ መጀመር የግድ እንደሚላቸው የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

ያደጉ ሀገራት ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ሕጎችና መመሪያዎች በልካቸው መቀየር ላይ ተጠምደዋል፡፡ ያደጉ ሀገራት የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጎታቸው ቅድሚያ ከመስጠታቸው በተጨማሪ በአየር ንብረት ለውጥ ለሚፈጠረው ጉዳት እራሳቸውን ከተጠያቂነት ነጻ ለማድረግ ሲጥሩ ይስተዋላል የሚሉት የአየር ንብረት ለውጥ ተሟጋችና ተመራማሪ ኑሃሚን ጥበቡ ፤ እራስን ብቻ የማዳን አካሄድ ባላደጉ ሀገራት ላይ ፖለቲካዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል ይላሉ፡፡

እንደ ተመራማሪዋ ገለጻ፤ ባደጉ ሀገራት መካከል ትብብር ባለመኖሩ በዋናነት በአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ በሚያስከትለው ጉዳት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ሕዝቦች በአየር ንብረት ለውጥ ተጠቂ ሆነዋል፡፡ እንደ ኮፕ29 ያሉና ሌሎች በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ የሚካሄዱ ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች ከወረቅት የዘለሉ አይደሉም፡፡ አፋጣኝ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅም በኢኮኖሚ ሽፋን ለማለፍ ተጨባጭ ባልሆነ ድርጊት አግበስብሰው ተግባራዊነቱም የውሃ ሽታ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል ሀገራት የተለያዩ ንቅናቄዎች መጀመር እንዳለባቸው ጠቅሰው፤ የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራና በታዳሽ ኃይል እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ለችግሩ መፍቻ ቁልፍ ነው፡፡ መሪዎችና የተለያዩ ተቋማት በአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ወቅት ግንኙነታቸውን የበለጠ በማጠናከር በዘርፉ ያላቸው ልምድና ተሞክሮ ልውውጥ እንዲሁም ተግባር ተኮር ድርጊት ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባቸዋል ነው ያሉት፡፡

የዘርፉ ባለሙያዎችና ተፅእኖ ፈጣሪ አካላት ያደጉ ሀገራት ትኩረት እንዲሰጡና ቃላቸውን ተፈጻሚ እንዲያደርጉ የማሳመን ሚናቸውን ማጠናከር አለባቸው። ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ለአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳ ላይ በመሥራት የተረጋጋችና ፍትሃዊነት የሰፈነባት ዓለም ለመፍጠር መትጋት አለበት ይላሉ፡፡

በኢትዮጵያ የኮንሰርተም የአየር ንብረት ለውጥ ጥበቃ ዳይሬክተርና ባለሙያ አቶ ዮናስ ገብሩ በበኩላቸው የሚደርሰው ጉዳት በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ያደጉ ሀገራት ተገቢውን ኃላፊነት ካለመወጣታቸው የመነጨ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎቻቸው ለአየር ንብረት ለውጥ የሚያበረክቱት አሉታዊ ተጽዕኖ ሀገራቱ ተመጣጣኝ ካሳ መክፈል እንዳለባቸውም ነው የገለጹት፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ባደጉ ሀገራት ጉዳት በሚያደርስበት ጊዜ የቴክኖሎጂ፣ የኢኮኖሚ ልዕልና ያላቸው በመሆኑ በትክክል እንደሚቆጣጠሩት አስታውሰው፤ ያላደጉ ሀገራት በተቃራኒው በከፍተኛ ደረጃ ተጎጂ እየሆኑ ነው፡፡ ለአብነትም ከአንድ መቶ ሺህ በላይ በቅርብ ጊዜ በተሠሩ ጥናቶች 80 በመቶ የሚሆነው የዓለም መሬትና ሰባት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ሕዝብ በአየር ንብረት ለውጥ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል፡፡

ባደጉ ሀገራት ለአየር ንብረት ለውጥ መከላከያ የሚደረጉ የገንዘብ ድጋፎች እንደ ብድር መታየት የለባቸውም የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ተግባራዊነታቸው ደካማ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በአየር ንብረት ለውጥ ይበልጥ ተጎጂ የሆኑ ሀገራት በተለያዩ ዓለም አቀፍ ጉባዔዎች የተገባላቸውን ቃል ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግና የአየር ንብረት ለውጥ ለመቀነስ አስፈላጊው አማራጭ መከተል እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡

አየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ ቃል የተገቡ ድጋፎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ብሎም ተጠያቂነትን ለማስፈን አፍሪካም ሆነ ሌሎች በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት በጋራ ድምጻቸውን ማሰማት የግድ እንደሚላቸው ይናገራሉ፡፡ የፋይናንስ ድጋፉ እንደ ስጦታ ብቻ ሳይሆን እንደ ግዴታም መታየት አለበት ባይ ናቸው፡፡

አፍሪካ በዓለም አየር ንብረት ለውጥ የምታደርሰው ጉዳት ዝቅተኛ ቢሆንም በከፍተኛ ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥ የምትጎዳ አሕጉር መሆኗን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

እኤአ በ2022 በአፍሪካ ከ110 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕዝቦች በቀጥታ በአየር ንብረት ለውጥ ተጎጂ ሆነዋል፡፡ በዚህም ከስምንት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ጉዳት በኢኮኖሚው ላይ ደርሷል፡፡ እንዲሁም አምስት ሺህ የሚጠጉ ሰዎች በድርቅና ጎርፍ ሳቢያ ለሞት መዳረጋቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ይህን አሳሳቢ የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከልና ለመቀነስ የበለጸጉ ሀገራት የገቡን ቃል ተግባራዊ እንዲያደርጉ ግፊት ከማድረግ ባሻገር እንደ ኢትዮጵያ አረጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ አተኩሮ መስራት እንደሚያስፈልግ ምሁራኑ ምክረ ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡

# አገልግሎቱ የውጭ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የምንቆጣጠርበት ሲስተም አለመኖሩ ችግሩን እንዲባባስ አድርጎታል ብለዋል፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት በሀገር ውስጥ ያሉ የውጭ ሀገር ዜጎችን የመመዝገብ ሥራ ተጀምሮ እንደነበር አስታውሰው፤ ቁጥራቸው በጣም ብዙ በመሆናቸው በሙሉ ለሙሉ ለመመዝገብ እንዳልተቻለ ተናግረዋል፡፡ በቀጣይ ጊዜያት ግን በሀገሪቷ ውስጥ ያሉ የውጭ ሀገር ዜጎች በሙሉ ለመመዝገብ ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

እየጎለበተ ያለው ሲስተም ወደ ሀገሪቱ የሚገቡና የሚወጡ ዜጎች ላይ ለመቆጣጠር ያስችላል የሚሉት አቶ አዳነ፤ በቀጣይ የውጭ ሀገር ዜጎች ለመመዝገብና ሕጋዊ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡

ሥርዓቱ ተግባራዊ ሲደረግ አንድ የውጭ ሀገር ዜጋ ሀገሪቷ ውስጥ የተፈቀደለት ጊዜ ሲያልቅ እንዲወጣ የሚያደርግ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም ሕገ ወጥነት እንዳይስፋፋና ሕጋዊነት እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል፤

አሁን ላይ ሥርዓቱ ዝግጅት እየተጠናቀቀ መሆኑን ገልጸው፤ በአሠራር ሁሉም ነገሮች መስመር ለማሲያዝ እየተሠራ እንደሆነ አመልክተው፤ ሥርዓቱ ማንኛውም ሰው ከተፈቀደለት ጉዳይ ውጪ ሌላ ነገር ላይ እንዳይሰማራ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን አመላክተዋል።

ሕገወጥ የውጭ ሀገር ዜጎች ከመቆጣጠር አንጻር ከሌሎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት ሥራዎች እንደሚሠሩ ተናግረዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ድጋፍ የበዛ ምስጋና የሚቸረው ነው!

በኢትዮጵያና በፈረንሳይ መካከል ያለው የዲፕሎማሲ ግንኙነት መቶ ሃያሰባት ዓመታትን ያስቆጠረ ስለመሆኑ የታሪክ መዛግብት ያመለክታሉ። በነዚህ ሰፊ ጊዜያት ውስጥም የሀገራቱን ብሄራዊ ጥቅሞች ታሳቢ ያደረጉ ዘርፈ ብዙ የትብብር ግንኙነቶች ተፈጥረዋል።

እነዚህ የትብብር ግንኙነቶች ባለፉት አምስት ዓመታት ከትብብር ግንኙነቶች አድገው ሁሉን አቀፍ ወደሆነ ስትራቴጂክ አጋርነት እየተለወጡ መጥተዋል። ይህም በአዲስ የለውጥ እና የዕድገት ምዕራፍ ውስጥ ላለችው ሀገራችን ትልቅ አቅም እየሆነ ይገኛል።

በተለይም የፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በተሻለ መልኩ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት፤ ወዳጅነትን እና የጋራ ተጠቃሚነት መሠረት ባደረገ መንገድ ፤ ወደ አዲስ ታሪካዊ ስትራቴጂክ አጋርነት እያሸጋገረ ነው።

ላለፉት አምስት ዓመታት በፈረንሳይ መንግሥት በኩል የኢትዮጵያ ባህር ኃይልን እንደገና ለማደራጀት፤ የኢትዮጵያ ቅርሶችን ለመጠበቅና ለማደስ ፣ የኢፌዴሪ አየር ኃይል ሙዚየምን ለማደራጀት የተገቡ ቃላትና እና በተግባር እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች ማሳያ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው። በሀገራቱ መካከል መተማመንን እና ላቅ ያለ ወዳጅነትንም ፈጥሯል።

መንግሥታቸው የኢትዮጵያውያን የለውጥ ፍላጎት መሠረት ያደረጉ ፖሊሲዎችን እና የልማት ፕሮጀክቶችን ከመደገፍ ባለፈ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገራቸው ያላትን ተደማጭነት በመጠቀም ለጀመርነው ሀገራዊ የብልጽግና ጉዞ ተጨማሪ አቅም ሆነዋል።

ከለውጡ ማግሥት እንደ ሀገር የጀመርነውን ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ በገንዘብ ከመደገፍ ጀምሮ ለስኬታማነቱ ቴክኒካዊ ፍጋፍ በመስጠት ላይ ናቸው። ሀገራችን ከአይ ኤም ኤፍ፣ ከዓለም ባንክ እና ከአውሮፓ ኅብረት የሚያስፈልጋትን የልማት ሀብት በማፈላለግም አጋርነታቸውን በተጨባጭ እያሳዩን ነው።

ሀገራቸው እና ሕዝባቸው ለታሪክ ከሚሰጡት ከፍ ያለ ዋጋ አንጻርም በእድሳት ማጣት ምክንያት አደጋ ውስጥ ገብቶ የነበረውን የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን የማደስ ሥራ እንዲከናወን በማድረግ ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶች ያላቸውን ከበሬታ በተግባር አሳይተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ሰሞኑን ታድሶ ወደ ሥራ የገባውን የታላቁን ቤተመንግሥት የእድሳት ሥራ የአንበሳውን ድርሻ በመውሰድ ፤ ቅርሶችን ወደ ዘላቂ ሀብትነት መለወጥ የሚችሉበትን ተሞክሮ በተግባር ማየት የቻልንበትን ዕድል ፈጥረው አሳይተውናል።

ከዚህ ተጨባጭ የሀገራቸው ኢንቨስተሮችን ጨምሮ ሌሎች የአውሮፓ ሀገራትን በማስተባበር በወሳኝ መስኮች ላይ ከኢትዮጵያ ጋር አብሮ ለመሥራት ቃል ገብተዋል። የፕሪቶሪያ ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ለማድረግ ለሀገራችን ዘላቂ ሰላም ያላቸውን አጋርነት አሳይተዋል።

በጦርነት የተጎዱ ሆስፒታሎችን መልሶ መገንባት፤ የሽግግር ፍትህ እና የሕግ የበላይነት ተግባራዊ እንዲሆን የሚያስፈልገውን ድጋፍ እንደሚሰጡ ተናግረዋል። የባሕር በር መኖር አስፈላጊነት ሆነ ይህንን ማመቻቸት አስፈላጊነት አምነው ሀገራቸው ባላት አቅም ማድረግ የምትችለውን እንደምታደርግ ቃል ገብተዋል።

በፕሬዚዳንት ኢማኑኤል በራሳቸው እና በመንግሥታቸው በኩል ፤ ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ዕድገት እያበረከቱ ያለው በመላው ኢትዮጵያውያን እውቅና የተቸረው አዲስ የትብብር ምዕራፍ ጅማሬ ነው። ለዚህ የአውነተኛ ወዳጅነት ተግባርም የበዛ ምስጋና ሊቸረው ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ስኬታማ ዲፕሎማሲ- ለብሄራዊ ጥቅም

መክሲተ-ወርቅ

ኢትዮጵያ ቀደምት ከሚባሉ ሀገራት አንዷናት። ይቺ ሀገር በአፍሪካ ታላቅ እና ተስፋ ያላት ሀገር ነች። ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር የተሸከመች እና ፈጣን ኢኮኖሚ የምታንቀሳቅስም ነች፡፡ የኢትዮጵያ ሰላም መሆን ለቀጣናው ሰላም እና ብልጽግና ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ኢትዮጵያ ባላት ጂኦፖለቲካዊ አቀማመጥና በቀጣናው ባላት ከፍተኛ ተደማጭነት የተለያዩ ሀገራት ለወዳጅነት ይመርጧታል፡፡

ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት መንግሥታት ሲቀያየሩባት የነበረ ቢሆንም በዲፕሎማሲው ረገድ እስካሁን የተሳካላት ሆና ቆይታለች፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር ለ127 ዓመታት የቆየ ወዳጅነቷ ነው፡፡ የበለጠ ተጠናክሮ ለትውልድ እንዲሻገርም እየተሠራበት ይገኛል፡፡

የፈረንሳይ መንግሥት ለኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ ቆይቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በባቡር መሠረተ ልማት፤ በትምህርት፤ በጤና፣ እና በቅርስ ጥበቃ ያደረጋቸው ድጋፎች በአበይትነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

> **የፈረንሳይ መንግሥት ለኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ ቆይቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በባቡር መሠረተ ልማት፤ በትምህርት፤ በጤና፣ እና በቅርስ ጥበቃ ያደረጋቸው ድጋፎች በአበይትነት የሚጠቀሱ ናቸው**

ከቅርስ ጥበቃ ጋር ተያይዞ የኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት ለማደስና አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ ለማድረግ ፈረንሳይ የአንበሳውን ድርሻ ወስዳለች፡፡ የተሠራው ሥራም የማደስ ብቻ ሳይሆን ቦታው ለጎብኚዎች ክፍት እንዲደረግ የሚያደርግም ነው። ፈረንሳይ ለኢትዮጵያ ቅርሶች ድጋፍ ያደረገችው ለቤተ-መንግሥቱ ብቻ አልነበረም፡፡ የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት እና እዚያ አካባቢ ያሉ አጠቃላይ ሥራዎችን ለማደስ እና ወደሚገባው ደረጃ ለማምጣት የፋይናንስ እና የቴክኒክ ድጋፍ አድርጋለች፡፡

የፈረንሳይ መንግሥት ፕሬዚዳንት ከዚህ ቀደም እ.ኤ.አ በማርች 2019 ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር፡፡ በመጀመሪያው ጉብኝታቸው በጣም ትልልቅ ፕሮግራሞች ከኢትዮጵያ ጋር አብረው እንደሚሠሩ ቃል ገብተው ነበር። በዚያን ወቅት በተደረገው ስምምነት ከላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት እድሳት ጋር በተያያዘ የተለያዩ ቡድኖች ተመሥርተው ነበር። ይህ በዓለም የመጀመሪያ ልንለው የምንችል የተለየ የትብብር ፕሮግራም ነበር። የእድሳቱ ሥራ አሁን ላይ ሃምሳ ከመቶ ገደማ ላይ ይገኛል ፤ቀሪውን ሥራ በሚቀጥሉት ጊዜያት በማጠናቀቅ ወደ ሥራ እንዲገባ ከመግባባት ላይ ተደርሷል።

እንደሚታወቀው ፈረንሳውያን ለባህል እና ለቅርስ ትልቅ ቦታ የሚሰጡ ሕዝቦች ናቸው፡፡ በቅርቡ የእሳት አደጋ የደረሰበትን የኖተራንዳም ቤተክርስቲያናችንን እንደ አዲስ አድሰው ለሕዝብ ክፍት ማድረግ ችለዋል። ለላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትም የገንዘብ፣ የቴክኒክ እና የባለሙያዎች ድጋፍ አድርገዋል፡፡ በሥራው ትላልቅ ትውልደ ፈረንሳውያን አርክቴክቶች፤ የተለያዩ እውቀት ባለቤቶች ፣ የሙዚየም እድሳት ባለሙያዎችን ልከው በሥራው ላይ የአቅማቸውን ማበርከት ችለዋል፡፡

ከዚህ ውጪ በቅርቡ ኢትዮጵያ ያካሄደችው የኢኮኖሚ ሪፎርምም በፈረንሳይ እና በቻይና የሚደገፍ ፕሮግራም ነው። ይህ ፕሮግራም እንዲሳካ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን በጣም ከፍተኛ ድጋፍ ለኢትዮጵያ እና ለሪፎርሙ አድርገዋል፡፡ ለዚህም ከፍተኛ ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል። በአውሮፓ ህብረት እና በአይ ኤም ኤፍ መድረክም የፈረንሳይ ድጋፍ አይተኬ ነበር፡፡

ከዚህ ውጪ የፈረንሳይ መንግሥትና ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ዋነኛ ኢንቨስተር በመሆን ሌሎች የአውሮፓ ሀገራትን በማስተባበር እንደምትሠራ ከመግባባት ላይ መደረሱ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፕሬዚዳንቱ ጋር በዝርዝር የተወያዩባቸውና የኢትዮጵያ የዘመናት እና የህልውና ጥያቄን ሊያስመልስ የሚችለው በሰላማዊ መንገድ የቀይ ባሕር ተጠቃሚ መሆን የሚለው ነጥብ ለትውልድና ለሀገር መሠረት ነው፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ130ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሀገር ናት፡፡ ኢኮኖሚዋ በፍጥነት እያደገ ያለበት ሁኔታ አለ፡፡ በዚህም ሀገሪቷ የባህር መውጫ ያስፈልጋታል። በዓለም ሕግ ፣በሰላማዊ እና በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እንደ ፈረንሳይ ያሉ ወዳጅ ሀገራትን ተጠቅመን ይህንን ፍላጎታችንን ማሳካትም ይኖርብናል፡፡

ኢማኑኤል ማክሮን ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጋር ባደረጉት ውይይትም የባሕር በር መኖር አስፈላጊነት እና ይህንን ማመቻቸት ተገቢ ጥያቄ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል። ፈረንሳይም ባላት አቅም ማድረግ የምትችለውን ድጋፍ እንደምታደርግ፤ በምን መንገድ? ለሚለው በንግግር እና በውይይት ፤ዓለም አቀፍ ሕጎችን እና ጎረቤት ሀገራትን ባከበረ ፤ ለኢትዮጵያ እና ለክልሉ በሚጠቅም መልኩ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል። የኢትዮጵያም ጥያቄ እሳቸው እንደሚሉት በሰላማዊ መንገድ የባሕር በር ማግኘት ነውና በዚህ ዙሪያ ያሉንን ወዳጅ ሀገራት በየጊዜው እየጠራን ውይይት ማድረግና ዓላማውን ማስረዳት ተገቢ ነው፡፡

ከኢኮኖሚ ምጣኔ ሀብት ጋር በተያያዘ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጋር በተነጋገሩት መሠረት እ.ኤ.አ በማርች 2019 በመጡ ጊዜ በሀገሪቱ ለተጀመረው ታላቅ የኢኮኖሚ ሪፎርም ድጋፍ ሰጥተዋል፡፡ የተለያዩ የቴክኒክ ድጋፎችን አድርገዋል። በቀጣይም ሌሎች ድጋፎችን እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል፡፡ ከኤሌክትሪክ ኔትወርክ ጋር በተያያዘ የፈረንሳይ ድርጅቶች መግባት የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል። ከእዳ ጋር በተያያዘም ከጂ 20 እና ከቻይናም ጋር የሚሠራ ሥራ ይኖራል።

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ የፈረንሳይ ድርጅቶች የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ስለመገኘቱም ተጠቅሷል፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ ሰላም ማስፈን ይቻል ዘንድ የፕሪቶሪያ ስምምነት ትልቅ ርምጃ ነው፡፡ ለዚህም ስምምነቱን ለማሳካት ከፈረንሳይ ጋር እየተሠራ ነው። ፈረንሳይም የስምምነቱ ተግባራዊነት እየደገፈች ትገኛለች፡፡

በተጨማሪም ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን በውይይታቸው ወቅት እንደገለጹት እርሻን ማበረታታት፤ የተጎዱ ሆስፒታሎችን መልሶ መገንባት፤ ከዛም በተጨማሪ የሽግግር ፍትህ ተግባራዊ የሚሆንበትን እና የሕግ የበላይነት የሚከበርበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ ድጋፍ እንደሚሰጡ ተናግረዋል፡፡ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትርን በቱርክ ከሶማሊያው ፕሬዚዳንት የሰላም ንግግር ማድረጋቸውን እንደሚደግፉትም ገልጸዋል፡፡ ታዲያ ይህ አይነቱ ትብብርና ትስስር የብሄራዊ ጥቅምን የሚያረጋግጥ ነውና ከሌሎች ወዳጅ ሀገራትም ጋር በተመሳሳይ መንገድ ሊሠራ ይገባል መልዕክቴ ነው፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ማኅበረሰባዊ ቅቡልነት መፍጠር የሚሻው - የፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት!

ዳንኤል ዘነበ

አንድ ማኅበረሰብ የቴክኖሎጂ እድገትን በየትኛውም ደረጃ ለማምጣት በመጀመሪያ የባሕል ዝግጅት እንደሚያስፈልገው የዘርፉ ታሪክ ተመራማሪዎች ይናገራሉ። የሀገራት ሥልጣኔም ቴክኖሎጂን በባሕላቸው ለመጠቀም ካላቸው ዝግጁነት እና ፍላጎት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። ስለሆነም ማንኛውም ቴክኖሎጂ፣ ፈጠራና አዳዲስ አሠራር በማህበራዊና፣ ሥነልቦናዊ ዝግጅት መደገፍ ይኖርበታል። በዚህ መንገድ መጓዝ ካልተቻል የቴክኖሎጂዎች ትግበራዊ ማኅበረሰባዊ ቅቡልነትን እንደሚያጣ ምሁራኑ ይገልፃሉ።

ዓለማችንን የለወጡ እንደ ስልክ፣ ኤሌክትሪክ (ELECTRICITY)፣ ክትባት (VACCINATION)፣ መኪና፣ አውሮፕላን እና መሰል የቴክኖሎጂ ውጤቶች አሁን ያላትን መልክ እንድትጎናጸፍ አድርገዋታል፡፡ በዘመኑ በነበረው ማኅበረሰብ ዘንድ ባሕላዊ ዝግጁነት ባለመኖሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶቹ ማህበረሰባዊ ተቃውሞ አስተናግደዋል። ለአብነት የስልክ ቴክኖሎጂ እንጥቀስ። የስልክ ቴክኖሎጂ በ1868 ዓ.ም. በተፈጠረባት አሜሪካም ስልክን ከጥንቆላና፣ ከአስማት ጋር በማያያዝ ሰፊው ማህበረሰብ እስኪጠቀመው ጊዜ ፈጅቷል። አንዳንዶቹ እንደ ተፈጥሯዊ ያልሆኑ ግዑዝ ነገር ሲቆጥሯቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ የሰይጣን ሥራ በማለት ያጣጥሏቸው ጭምር ነበር።

በኢትዮጵያ የዘመናዊነት ጉዞ አዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ያለው አመለካከትና ፍላጎት አለመኖር ከዚህ የተለየ እንዳልነበር ታሪክ ይናገራል። ሀገሪቷን ለማዘመን የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን በመተለም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስገባት፣ በራስ አቅም የማምረት ራዕይ በመያዝ ጥረት ሲያደርጉ ነበር። ራዕዩን ለማሳካት በሚያደርጉት ጥረት ውጫዊ እና ውስጣዊ ፈተናዎችን ተጋፍጠዋል። በዚህ ረገድ ፈተናውን ተቋቁመው በተሳካ ሁኔታ ኢትዮጵያን ወደ ዘመናዊነት ማሸጋገር የቻሉት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ እንደነበሩ በታሪክ ተጽፏል።

ጳውሎስ ኞኞ "አጤ ምኒልክ" በሚለው መጽሐፉ ንጉሡ ጥንታዊ ሥልጣኔዎችን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ምን ያህል ችግርና ፈተና ደርሶባቸው እንደነበር ገልጾታል። በዘመናዊት ኢትዮጵያ፣ በቴክኖሎጂ ረገድ በተደረገው ግሥጋሴ ፊት አውራሪ መሆናቸውን በመጥቀስ ፤ አጼ ምኒልክም በወቅቱ በዓለም ዙርያ አሉ የተባሉት የጥበብና የፈጠራ መገለጫ አገልግሎቶችና ቁሳቁሶች ወደ ኢትዮጵያ አስገብተዋል። የዘመናዊ ሥልጣኔ ራዕይ ይዘው የተነሱት ንጉሡ በመጀመሪያው ማዕበል ወደ ከተማዋ የመጡት ባቡር፣ ባንክ፣ ጥይት ፋብሪካ የስልክ መስመር፣ ቴሌግራፍ፣ ወፍጮ፣ በእንፋሎት የሚሄድ ሞተር እና ሌሎችም ሲጠቀሱ፤ በሁለተኛው ዙር ከገቡት የፈጠራ ውጤቶች መካከል ደግሞ ቴያትር ቤት፣ መኪና፣ የቧንቧ ውሃ፣ ሆቴል እና በርካታ ትናንሽ ቁሳቁሶች ይገኙበታል። ንጉሡ በዘመኑ ቴክኖሎጂዎቹ ወደ አዲስ አበባ በገቡበት ወቅትም ከማህበረሰቡ ከፍተኛ ተቃውሞ ይገጥማቸው እንደነበር በመጽሐፉ አመላክቷል።

ጳውሎስ ኞኞ ፤ አንዳንዶቹ እንደ ተፈጥሯዊ ያልሆኑ ግዑዝ ነገር ሲቆጥሯቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ የሰይጣን ሥራ በማለት ያጣጥሏቸው ነበር። ስለሆነም አብዛኞቹ ፈጠራዎች በንጉሱ ጥብቅ ክትትልና የበላይ ጠባቂነት በቤተ - መንግሥቱና በአራት ኪሎ አካባቢ ከማህበረሰቡ ጋር የመጀመሪያ ትውውቃቸውን አድርገዋል። በዚህም አጼ ምኒልክ የቴክኖሎጂ ባሕላዊ ቅቡልነት እንዲያድግ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ እንደ ልዩ ነገር በጥርጣሬ ይታይ ከነበሩት ቴክኖሎጂዎች መካከል ስልክ ዋነኛው ነበር ይላል።

በወቅቱ የሰውነት አካል የሌለውን ድምጽ መስማት በአካባቢው ቀሳውስቶች ዘንድ ፍርሃትን የፈጠረና እንደክፉ መንፈስ ሥራ የተቆጠረ ነበር። በዚህ ምክንያት ስልክ ከቤተክህነት አካባቢ ከፍተኛና የአደባባይ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር። በቤተመንግሥት ውስጥ ያሉ ቢሮዎችን ለማገናኘት የስልክ መስመር መዘርጋት ሲጀምር ከቤተክርስቲያን በተላኩ ቄሶች አማካኝነት የሰይጣን ሥራ ስለሆነ መሳሪያው እንዲወገድ የሚል ቅሬታም ቀረበ።

በዘመናዊት ኢትዮጵያ፣ በቴክኖሎጂ ረገድ በተደረገው ግሥጋሴ ፊት አውራሪ የሆኑት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ የሕዝቡን ችግር በማሰብ የእህል ወፍጮ ወደ ሀገራችን እንዲገባ ሲያደርጉ ትልቅ ተቃውሞ ገጥሟቸዋል እንደነበር መጽሐፉ ያስረዳል። 'የእህል ወፍጮ የሚፈጨው በጋኔል ነው' እያለ ሕዝቡ በውኃ መዘውር በሚንቀሳቀስ ወፍጮ እህል አላስፈጭ ቢላቸው ወፍጮው ጋኔል አለመሆኑን ለማሳየት ዱቄት አስፈጪ ሆነው እስከ መሥራት መድረሳቸውን ጳውሎስ ኞኞ ጽፏል። በዘመኑ የዳግማዊ አጼ ምኒልክ የቴክኖሎጂ ጥማት እና ከማህበረሰቡ ንቃት ጋር ባለመጣጣሙ ዘመናዊ ሥልጣኔን የማስፋፋት ርምጃውን ፈታኝ እንዳደረገው መረዳት ይቻላል።

በዚህ ዘመንም በሀገራችን አዳዲስ ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞከር ተመሳሳይ እንቅፋቶች ይገጥማሉ። ለዚህ ደግሞ በ2015 ዓ.ም በኢትዮጵያ መተግበር የጀመረው "ፋይዳ" ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ለአብነት ይጠቀሳል። አሁን ባለንበት የዲጂታል ዓለም አንድ ሰው ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ለማንነቱ ማሳወቂያም መተማመኛም ማስፈለግ ከጀመረው ሁለት አስርት ዓመታት ማስቆጠሩ ይታወቃል። በርካታ ሀገራት የዘመናዊ መታወቂያን ፋይዳ በመረዳት በርካታ ሀገራት የዲጂታል መታወቂያን በሚመለከት ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፈው፣ ሕግ አውጥተው ወደ ተግባር ተሸጋግረዋል። እንደ ኢስቶኒያ ያሉት ሀገሮች ደግሞ በአስደማሚ ብቃትና ውጤታማነት ተግባራዊ በማድረግ ለበርካታ ሀገሮች አርዓያ ሆነዋል፡፡ ህንድ ከአጠቃላይ ሕዝቧ 1 ነጥብ 2 ቢሊዮን የሚሆነው ዲጂታል መታወቂያ አለው፡፡ የቀራት 100 ሚሊዮን የሚሆን ብቻ ነው፡፡

ቢዘገይም በኢትዮጵያ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለፀገ፣ ዘርፍ ተሻጋሪ፣ መሠረታዊ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ለመዘርጋት ጥረት እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል። በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የ'ፋይዳ' ዲጂታል መታወቂያን ተደራሽ ለማድረግ ከኢትዮ-ቴሌኮም፣ ከጤና፣ ከትምህርት፣ ከፋይናንስ ተቋማትና ከሌሎችም ጋር በጥምረት እየሠራ ይገኛል።

በአሁን ወቅት ለ10 ሚሊዮን ዜጎች የፋይዳ ዲጂታል መታወቂያን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። ይሁንና ከታቀደው አንጻር አፈጻጸሙ የሚፈለገውን ያህል እንዳልሆነ የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ አስታውቋል። ይህም በማኅበረሰቡ ዘንድ በተፈጠረ የተሳሳተ የአመለካከት ችግር ሊከሰት እንደቻለ ይፋ አድርጓል። በኅብረተሰቡ ዘንድ የ'ዲጂታል መታወቂያ ከሃይማኖት አስተምህሮት ጋር የሚጣላ ነው' የሚል አመለካከት መኖሩን ለመረዳት ተችሏል። ይሁንና የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ከሃይማኖት አስተምሮ ጋር ምንም ዓይነት ተቃርኖ የለውም።

በአንድ መድረክ ላይ የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ፀሐፊ ቀሲስ ታጋይ ታደለ እንዳረጋገጡት፤ ፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ከሃይማኖት አስተምሮ ጋር ከመቃረን ይልቅ፤ ከሃይማኖታዊ አስተምሮት ጋር የሚጣጣም ሥርዓት ነው። ዲጂታል መታወቂያ በማኅበረሰብ መካከል እርስ በእርስ መተማመን የሚፈጥርና ፍትሐዊነት የሚለውን ሃይማኖታዊ አስተምህሮን የሚከተል፤ ሀገራዊ ልማትን ለማረጋገጥ፣ ወንጀልን ለመከላከል የሚረዳም ጭምር እንደሆነ ገልጸው፤ ይህም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ከሃይማኖት አስተምሮ ጋር ምንም ዓይነት ተቃርኖ እንደሌለው ነው ቀሲስ ታጋይ ያስታወቁት። ይሁንና ፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ በአብዛኛው ማኅበረሰብ ዘንድ በግንዛቤ እጥረትና የተሳሳተ አመለካከት የተነሳ ተደራሽነቱ አናሳ እንደሆነ ተነግሯል። በተለይ በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ማኅበረሰቡ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ፣ እንዲጠራጠር የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

**ታዋቂ ሰዎች ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች የሀገር ሽማግሌዎች በማሳተፍ ሀገራዊ ንቅናቄ በማድረግ መታወቂያው ሀገራዊ ልማትን ለማሳደግ፣ ማጭበርበርንና ወንጀልን ለመከላከል እንዲሁም ቀልጣፋ አገልግሎት ለማግኘት የሚረዳ መሆኑን ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል**

በመግቢያችን እንደገለጽነው፤ የሀገራት ሥልጣኔም ቴክኖሎጂን በባሕላቸው ለመጠቀም ካላቸው ዝግጁነት እና ፍላጎት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑን ሊታወቅ ይገባል። ማንኛውም ቴክኖሎጂ፣ ፈጠራና አዳዲስ አሠራር በማህበራዊና፣ ሥነ ልቦናዊ ዝግጅት መደገፍ እንዳለበት ይታመናል። የብሔራዊ መታወቂያ ሥርዓት ትግበራው ስኬታማ ለማድረግ ማኅበረሰባዊ ቅቡልነትን መፍጠር እንደሚገባ መታወቅ ይኖርበታል። ፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ ከሃይማኖት አስተምህሮት ጋር ተቃርኖ እንደሌለው በማስተማር ማኅበረሰቡ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላትን ጠንካራ ተሳትፎ ይጠይቃል።

በዚህም የመንግሥት አካላት ዲጂታል መታወቂያን በመውሰድ ለህብረተሰቡ ሞዴል ሆነው መታየት ይኖርባቸዋል። በዘመናዊት ኢትዮጵያ ጉዞ የአንበሳውን ድርሻ እንደያዙ የጠቀስናቸው ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ሕዝቡ ቴክኖሎጂዎችን እንዲቀበል ለማድረግ ሲሞክሩ የነበሩት በቃላት ሳይሆን በተግባር እንደነበር ይታወቃል። ከ'ሺህ ቃላት፤ አንድ ድርጊት' እንደሚባለው በዝርዝር የቀረቡትን የፋይዳን ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች በተግባር በተደገፈ ማሳያ ሕዝቡ እንዲያይ ማድረግ ያስፈልጋል። ለምሳሌ አገልግሎትን ከማቅለል አኳያ ያለውን ጥቅም በተግባር እንዲመለከት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከዚህ ባሻገር የህብረተሰቡ ግንዛቤ መጨመር የሚያስችሉ የንቅናቄ ሥራዎችን መሥራት እንዲሁም ዜጎች በተለያዩ ተቋማት አገልግሎት ለማግኘት ሲፈልጉ "ፋይዳ" ዲጂታል መታወቂያን መያዝ ቅድመ ሁኔታ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡

ሌላው የሃይማኖት አባቶች ጠንካራ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው። በሁሉም ቤተ እምነት የሚገኙ የሃይማኖት አባቶች የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱ ከሃይማኖት አስተምሮ ጋር ተቃርኖ የሌለው መሆኑን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እና ተዓማኒነት ባላቸው የሃይማኖት አባቶችን ምሳሌ በማድረግና በሚሰጡት አስተምሕሮ በመጠቀም ተደራሽነቱን ማስፋት ያስችላል። በመሆኑም የእምነት አባቶች በሃይማኖት ተቋማቸው የሚገኘውን ማኅበረሰብ በማስረዳት፣ ምሳሌ በመሆን እና በማስተማር እውነታውን በማሳወቅ ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል። ይህ የሃይማኖት አባቶች ተሳትፎ የሚፈጥረውን ተጽእኖ ከሦስት ዓመት በፊት በኮቪድ -19 ወረርሽኝ ወቅት ማሳያ ይሆናል።

ኮቪድ-19 በዓለም አቀፍ ደረጃ መከሰቱን ተከትሎ በርካታ ሰዎች በወረርሽኙ ሳቢያ ለውስብስብ የጤና ጉዳቶችና ለሞት ተዳርገዋል። በወቅቱ የሳይንሱ ጠበብቶች የኮቪድ 19 ክትባትን መፍጠር ቢችሉም፤ ቅቡልነቱ አጥጋቢ እንዳልነበር ይታወሳል። በተመሳሳይ በሀገራችን ክትባቱ ጋር ተያይዞ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ስለክትባቱ የሚጻፉ መረጃዎች በርካቶችን አሳስተዋል፤ ጥርጣሬ እንዲፈጠር ማድረጋቸው ይታወሳል። ይሁንና ህብረተሰቡ ክትባቱን እንዲወስድ የሃይማኖት አባቶች በመከተብ ጭምር ተፈጥሮ የነበረውን ጥርጣሬ ለማጥፋት ጥረዋል። በዚህም የሃይማኖት አባቶች በኮቪድ - 19 የክትባት ዘመቻው ውጤታማነት ትልቅ ሚና እንደነበራቸው ሁሉ በፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት መድገም ይኖርባቸዋል።

በተጨማሪም ታዋቂ ሰዎች ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች የሀገር ሽማግሌዎች በማሳተፍ ሀገራዊ ንቅናቄ በማድረግ መታወቂያው ሀገራዊ ልማትን ለማሳደግ፣ ማጭበርበርንና ወንጀልን ለመከላከል እንዲሁም ቀልጣፋ አገልግሎት ለማግኘት የሚረዳ መሆኑን ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል። ኅብረተሰቡ አገልግሎቱን በመጠቀሙ የሚያገኘውን ዘርፈ ብዙ ጥቅም በሚገባ ማወቅና መረዳት ከቻለ በአጭር ጊዜ የሚፈለገው ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ይታመናል።

በጥቅሉ ዘመናዊ የመታወቂያ ሥርዓት በአንድ ሀገር ውስጥ ተግባራዊ ሲደረግ መሠረታዊ የሚባሉ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይታመናል። የፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ በአዋጅ ቁጥር 1284/2015 በኢትዮጵያ ይፋ የሆነ መሠረታዊ ህጋዊ መታወቂያ የዲጂታል መታወቂያ ትግበራው ለሀገሪቱ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን፣ እንዲሁም ለአሥር ዓመቱ የመንግሥት የልማት ዕቅድ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

በአግባቡ የተተገበረ ዲጂታል መታወቂያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጠቅላላ ምርት (ጂዲፒ) ላይ እስከ ስድስት በመቶ የሚደርስ ጭማሪ ያለው አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚችል ይታመናል፡፡ በዚህም ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብቷንና የዜጎችንም የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ስለዚህ በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ዝርጋታ የሚገኘን የውጤት ፍሬ መብላት የሚቻለው የማኅበረሰቡን የተሳሳተ አመለካከት አስተካክሎ ጠንካራ ተሳትፎ ማድረግ ሲቻል እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን - በሀገር ልጅ

ወርቅነሽ ደምሰው

ካህሳይ ኃይለኪሮስ (ዶ/ር) ይባላሉ፡፡ በግብርናው መስክ የምርምር ሥራዎችን በመሥራት ሰባት ዓመታትን ያህል አሳልፈዋል፡፡ በተለይ የተፈጥሮ ማዳበሪያን ሀገር ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ግብዓቶች ለማምረት አስበው ምርምር ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ለዓመታት የደከሙበት ይህ የምርምር ሥራ ውጤታማ ሆኖም አራት ዓይነት የምርምር ውጤቶችን ማግኘት ችለዋል፡፡

የምርምር ሥራቸውን በመቀሌ ሲያደርጉ የቆዩት ዶክተር ካህሳይ፣ በተለይ የአፈር ለምነት ከመጠበቅ አንጻር ትኩረት ሰጥተው መመራመራቸውን ይገልጻሉ፡፡ የአፈር ለምነት ሊጠበቁ የሚችሉ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችንና ሌሎች ምርቶችን በምርምር አግኝተዋል፡፡

እነዚህ የምርምር ሥራዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ፋይናንስ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ለማግኘትም ለሁለት ዓመታት ያህል ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ያገኙትን አጋጣሚ ተጠቅመው የምርምር ሥራዎቻቸውን ለእይታ ካቀረቡ በኋላ ግን በተፈጠረላቸው የገበያ ትስስርና ባገኙት የሥራ አጋር በሙሉ አቅማቸው ወደ ሥራ ለመግባት የሚያስችላቸው እድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት አልትራ ኦርጋኒክ ፈርቲላይዘር እና ፔስቲሳይድ ፒኤልሲ(Ultra Organic Fertilizer and pesticides manufacturing plc) የተሰኘ ድርጅት መስርተዋል ፤ አራት ዓይነት ምርቶች ለማምረት የሚያስችል ሥራ አጠናቀዋል፡፡ እነዚህም አንደኛውና ጠጣር ማዳበሪያ(ሶሊድ ፈርቲላይዘር) የሚባለው ነው፡፡ ሁለተኛው ፈሳሽ ማዳበሪያ (ሊክዊድ ፈርቲላይዘር) ነው። እነዚህ የምርምር ውጤቶች በጠጣርና ፈሳሽ መልኩ የተዘጋጁ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች ናቸው፡፡

ሦስተኛው አርትራ ቴን ኮምፖስት ፋስሊቴተር (Ultra ten compost facilitator) የተሰኘውን የተፈጥሮ ማዳበሪያን/ኮምፖስትን/ በአስር ቀን ማምረት ይቻላል። አራተኛው ጸረ ተባይ /ፔስቲሳይድ/ ከተፈጥሮ የአፈር ማዕድናትና እጽዋት ተዋጽኦ የሚዘጋጅ ነው፡፡ አራቱም ምርቶች በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ግብዓቶች ይመረታሉ፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ሁሉም ምርቶች የራሳቸው አገልግሎቶች አላቸው፡፡ ፔስቲሳይድ (pesticides) የተሰኘው ምርት፣ ከአፈር ማዕድናትና እጽዋት ተዋጽኦ የሚዘጋጅ የጸረ ተባይ መከላከያ ነው፡፡ ጠጣርና ፈሳሽ ማዳበሪያ (ሶሊድና ሊኩዩድ ፈርቲላይዘር) ከጠጣር ወይም ደረቅና ፈሳሽ የተፈጥሮ ማዳበሪያ የሚሠራና የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ ጥቅም ላይ የሚውል ነው። አርትራ ቴን ኮምፖስት ፋስሊቴተር (Ultra ten compost facilitator )የተሰኘው ደግሞ ከእንስሳትና ከእጽዋት የሚገኙ ተረፈ ምርቶች ወደ ጥቅም የሚቀየሩበትን ሁኔታ የሚያፋጥን በመሆኑ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

ምርቶቹ ለአርሶ አደሩ እንዲቀርቡ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይ ደረቅ/ጠጣር/ የተፈጥሮ ማዳበሪያውን በሁለት ወራት ውስጥ ለማምረት መታቀዱን ጠቁመዋል፡፡ ማዳበሪያውን ለማምረት የሚያስችለው ፋብሪካ ግንባታ በማጠናቀቅ ወደ ማምረት ሥራ ለመግባት እየተሠራ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

እንደ ዶክተር ካህሳይ ማብራሪያ፤ የማዳበሪያ ዓይነቶቹ በምርምር የተገኙ እንደመሆናቸው ብዙ ነገሮች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅተዋል፡፡ ሁለቱንም የተፈጥሮ ማዳበሪያ ዓይነቶች ብንመለከት በተለያዩ የአፈር ዓይነቶች እና የአፈር ሁኔታ ላይ ምርምር ተካሄዶ የተዘጋጁ ናቸው። ፈሳሽ የተፈጥሮ ማዳበሪያውን ለመጠቀም ስንፈልግ አፈሩ አሲዳማ ከሆነ አፈሩ ላይ ሕክምና ማድረግ ይገባል፤ ማዳበሪያው ተገቢ የሚባሉ ንጥረ ነገሮችን እንዲይዝ ተደርጎ በሚገባ ታስቦበት የተሠራ ነው፡፡

እንደ ዶክተር ካህሳይ ገለጻ፤ የምርምር ሥራዎቹ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤትና በትግራይ ክልል ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ በኩል ምርምር ላይ እያሉ ተፈትሸው ውጤታማነታቸው ተረጋግጧል፡፡ ወደ ማምረት ሲገባ ደግሞ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትና የግብርና ሚኒስቴር በሚያዘጋጇቸው የሙከራ ቦታዎች ላይ ተሞክረው ትክክለኛነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ጥቅም እንዲውሉና ለገበያ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡




ካህሳይ ኃይለኪሮስ (ዶ/ር)

**የማዳበሪያ ዓይነቶቹ በምርምር የተገኙ እንደመሆናቸው ብዙ ነገሮች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅተዋል፡፡ ሁለቱንም የተፈጥሮ ማዳበሪያ ዓይነቶች ብንመለከት በተለያዩ የአፈር ዓይነቶች እና የአፈር ሁኔታ ላይ ምርምር ተካሄዶ የተዘጋጁ ናቸው**

‹‹ምርቶቹ ላይ ችግር እንዳይገጥምን በማሰብ ትክክለኛነታቸው በደንብ እስኪረጋገጥ ድረስ እስካሁን ምርቶቻችን ወደ ገበያ አልገቡም፡፡ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ተብሎ ብዙ ድርጅቶች ምርቶችን እያመረቱ ነው፡፡ ከእነርሱ ጋር መቀላቀል የለበትም፡፡ እኛም መንግሥት የሚያውቀው ማረጋገጫ ካገኘን በኋላ ወደ ገበያ እንገባለን በሚል እስካሁን ቆይቷል›› ይላሉ፡፡

የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች በሀገር ውስጥ ማምረት መቻል ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው የሚሉት ዶክተሩ፤ አሁን ላይ በሀገሪቱ እንደሚታየው ሰፊ የሆነ የማዳበሪያ የአቅርቦት እጥረት አለ፡፡ ይህ ምርት ወደ ገበያ ሲገባ እጥረት በመቅረፍ ረገድ ደጋፊ ይሆናል፡፡ ወደፊት ደግሞ የተፈጥሮ ማዳበሪያን ጥቅም አርሶ አደሩም ሆነ ህብረተሰቡ እያጎለበተውና ሙሉ ተጠቃሚ እየሆነ ይመጣል፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የአፈር ለምነት እየጨመረ አሲዳማነት እየቀነሰ ይመጣል፡፡ በመሆኑ ምርቶቹ ከአፈር ጋር ተያይዞ ለሚመጡ ብዙ ችግሮች መፍትሔ ሊሆን የሚችል እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡

አራቱም ዓይነት ማዳበሪያዎች ለአፈር ለምነት በእጅጉ ተፈላጊና ጠቃሚ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ቢሆንም ለሀገሪቱም ሆነ ለአርሶ አደሩ በእጅጉ ጠቃሚና ተመራጩ ደረቁ/ጠጣሩ/ የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይህን ማዳበሪያ ለማምረት የሚያስፈልገውን ፋብሪካ ከውጭ ለማስመጣት ግን ከፍተኛ ወጪ እንደሚጠይቅ አስታውቀዋል። በዚህ ላይ ብዙ ባለሀብቶች ኢንቪስት ለማድረግ ደፍረው እንደማይገቡም አመልክተው፣ ይህ ድርጅት ግን ፋብሪካ ለመገንባት ከአጋር አካላት ጋር እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ፋብሪካው በአዲስ አበባ እየተገነባ ነው፡፡ ለፋብሪካ የሚያገለግሉ ማሽኖች ከቻይና የመጡ ሲሆን፣ ግንባታውም በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ ግንባታው ተጠናቆ ወደ ሥራ ሲገባም በሰዓት አራት ሺ ኩንታል ማዳበሪያ ያመርታል፡፡ ሥራው በደንብ ከጀመረ በኋላ የማምረት አቅሙን በመጨመር 30ሺ ኩንታል በሰዓት እንዲያመርት ያደርጋል፡፡ በቋሚነት ለ30 ለሚሆኑ፣ በጊዜያዊነት ደግሞ ከ100 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡

ከጠጣር (ከደረቅ) የተፈጥሮ ማዳበሪያ ውጭ ያሉት ሌሎቹ ምርቶች እንደ ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ለአብነት አርትራ ቴን ማዳበሪያ ፋስሊቴተር ለደረቅ ተፈጥሮ ማዳበሪያ የሚውለው ተፈጥሯዊ የሆኑ የእጽዋት ውጤቶችን በአስር ቀናት ውስጥ ኮምፖስት እየሠራ ለማስገባት ይረዳል፡፡ ሁሉም ምርቶች ለሚቋቋመው የደረቅ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በግብዓትነት እንዲውሉ ተደርገው ከፋብሪካ ጥቅም አንጻር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

‹‹አሁን በገበያ ላይ ያሉ ከውጭ ሀገር የሚገቡ እንዲሁም ሀገር ውስጥ የሚመረቱ በርካታ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች አሉ፡፡ በተለይ ፈሳሽ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በብዛት በገበያ ላይ ይገኛል፡፡ በሀገር ውስጥ ብዙ ድርጅቶች ፈሳሽ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ያመርታሉ፡፡

እነዚህ ምርቶች ግን በሚጠቀሟቸው ነጥረ ነገሮችና ጥራት ይለያሉ፡፡ ብዙ የተፈጥሮ ማዳበሪያ የሚያመርቱ ድርጅቶች በሥራ አጋጣሚ አይተናቸዋል፤ ጥናቶችንም አድርገናል ሲሉ ዶክተር ካህሳይ፣ ‹‹የእኛን ምርት ከእነርሱ ለየት የሚያደርገው ምርቶቻቸው በኛ ልክ ተፈጥሯዊ ነጥረ ነገሮች የሌላቸው መሆኑ ላይ ነው፤ በጥራትም ቢሆን ከእኛ ሊወዳደሩ የሚችሉ አይደሉም›› ይላሉ፡፡፡

አሁን በሀገር ውስጥ የተዘጋጁት አራቱም ዓይነት ምርቶች በዋጋም ቢሆን ከሌሎች በገበያ ላይ ካሉት ተመሳሳይ ምርቶች አንጻር በግማሽ ያህል እንደሚቀንሱም ጠቁመዋል፡፡ ለወደፊት የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች ጠቀሜታ እየታወቀ ተፈላጊነቱ እየጨመረ ሲመጣ ተፈጥሯዊ የሆኑ ምርቶች ዋጋ እየተወደደ እንደሚሄድ ካህሳይ (ዶ/ር) አመልክተዋል፡፡ ‹‹አሁን ገበያውን ሰብሮ ለመግባትና ህብረተሰቡ ዘንድ ተደራሽ ለመሆን የምርቶቹን ዋጋ በ50 በመቶ ያህል በመቀነስ ወደ ገበያው ለመግባት እናስባለን ብለዋል፡፡

‹‹ወደ ማምረት ሂደቱና ገበያው ሳንገባ ከአሁኑ ከፍተኛ ፍላጎት እየታየ ነው፤ የምርት እጥረት እንዳይገጥመን እየሰጋንም እንገኛለን፤ በገበያ ላይ ምንም ዓይነት ችግር ይገጥመናል ብለን አናስብም ›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ምርቶቹ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ተሞክረው ውጤታማ መሆናቸውንም ጠቅሰው፤ አርሶ አደሮቹ ባዩት በእጅጉ መደሰታቸውን ካህሳይ (ዶ/ር) ገልጸዋል። የፋብሪካው ግንባታ እንደተጠናቀቀ ወደ ማምረቱ ሥራ በመግባት ምርቶቹን ለገበያ በማቅረብ የተፈጥሮ ማዳበሪያው ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል ሲሉ አስታውቀዋል፤ ይህ ሥራ ለሀገር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን ተናግረው፣ መንግሥት ለምርቶቹ ትኩረት እንዲሰጥ፣ ማህበረሰቡም ማዳበሪያዎቹን ተረድቶ ተጠቃሚ እንዲሆን እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

‹‹ከምርቱም በላይ ዋነኛ ዓላማችን የሀገሪቱ አፈር ለምነትና ጤናማነት እንዲስተካከል እንፈልጋለን፡፡ ለዚህም ሁሉም የግብርና፣ የሳይንስና ምርምር አካላትና የሚመለከታቸው ሁሉ ትኩረት ሰጥተው አብረውን ሊሠሩ ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን ቀጣይነት ባለው መልኩ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማምረት እንችላለን›› ብለዋል፡፡

የድርጅቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ሃየሎም ገብረጨርቆስ በበኩላቸው እንዳብራሩት፤ ድርጅቱ ተፈጥሯዊ ማዳበሪያዎችን ለማምረት እንቅስቃሴ ሲጀመር ብዙ ነገሮች ታሳቢ ተደርገዋል፤ የመጀመሪያ ትኩረት የተፈጥሮ /ኦርጋኒክ/ የሚለው ነው፡፡ ኦርጋኒክ ስንል ስለ ሰውና ስለአፈር መናገራችን ነው፡፡ የተፈጥሮ ማዳበሪያ /የአፈር ማዳበሪያ/ የአፈር ጤንነት ለመጠበቅ ይጠቅማል፡፡ የአፈር ጤንነት ለመጠበቅ ተፈጥሯዊ ምርቶችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ታምኖበት ሲሠራ ቆይቷል፡፡

በተጨማሪም ድርጅቱ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማዘጋጀት በሚወስደው ረጅም ጊዜ ላይ ለውጥ ማምጣት ችሏል። ይህንንም ለአብነት ጠቅሰው ሲያብራሩ፤ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማዘጋጀት ስድስት ወራት ይፈጅ የነበረበትን ሁኔታ ወደ አሥር ቀን ማውረድ ያስቻለ አርትራ ቴን ኮምፖስትን ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም ማንኛውም አርሶ አደር ሆነ ህብረተሰብ በየቤቱ ያለውን ተረፈ ምርት ጥቅም ላይ መዋል ያስችላል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

‹‹መሬት ልክ እንደ ሰው እንክብካቤ ይፈልጋል፤ ስለመሬት እንክብካቤ ካነሳን ደግሞ ከተፈጥሮ ማዳበሪያ ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ትልቁ ለመሬት በግብዓትነት የሚያገለግል በመሆኑ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው›› የሚለው ምክትል ሥራ አስኪያጁ፤ ይህንን ለማድረግ የግንዛቤና የትኩረት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየጓሮው ሊሠራው እንደሚችልም አስገንዝበዋል፡፡

ምክትል ሥራ አስኪያጁ እንዳሉት፤ የዶክተር ካህሳይ የምርምር ውጤት የሆነ ከተፈጥሮ የአፈር ማዕድናትና እጽዋት ተዋጽኦ የሚሠራው ጸረ ተባይ /አርተራ ቤስት ሳይድ/ 14 ዓይነት የጸረ ተባይ ምርምር ውጤት ይዟል። ይህ ጸረ ተባይ እንደ ሀገር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛው በመሆኑ ወደ ማህበረሰቡ ማስፋት ይገባል፡፡ በተለይ ለአርሶ አደሩ ወይም ለአምራቹ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ግብዓት ሊሆን ይችላል፡፡

አሁን አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂ የታገዘ ባይሆንም እንደ ተፈጥሮ ማዳበሪያ /ኮምፖስት/ ያሉትን እየሠራ ሲጠቀም ኖሯል የሚሉት ምክትል ሥራ አስኪያጁ፤ ይሄ ግን በምርምርና ፈጠራ የተደገፈ የአርሶ አደሩን ድካም ማቅለል ጊዜንና ወጪን መቀነስ የተቻለበት ነው ብለዋል፡፡

ይህም አርሶ አደሩ ብዙ ድካም ውስጥ ሳይገባ ጊዜውን ቆጥቦ እንዲሠራ እንደሚያስችል ጠቅሰው፤ ይሄን የምርምር ውጤት መንግሥትም ትኩረት ሰጥቶት ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ ማድረግ እንደሚኖርበት ገልጸዋል፡፡

# ወቅታዊ ትንታኔ

## የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እና ቀጣናዊ ፋይዳው

**ምሕረት ሞገስ**

የቀድሞ መንግሥታት የውጭ ግንኙነት እና የብሔራዊ ደህንነት ፖሊሲያቸውን ከጎረቤት ሀገር ጋር በፅኑ ሰላማዊ እና የጋራ ተጠቃሚነት ላይ ከመመሥረት ይልቅ፣ በጠላትነት መፈረጅ እና በጥርጣሬ ዓይን መመልከት ላይ ያተኮረ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተቃራኒው የአሁኑ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ላይ እንደተመላከተው፣ በብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት ላይ የሚሰነዘሩ አደጋዎችን መከላከል አስፈላጊ መሆኑ ቢታመንም፣ ወደ ውጭ ከመመልከት ይልቅ ውስጥን በማየት ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት ላይ የትብብር እድሎችን ማስፋት ቅድሚያ ይሰጠዋል። በዚህ ውስጥ ደግሞ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖር ሰላማዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ልዩ ትኩረት አግኝቷል።

ፖሊሲው ከምን አንፃር ለጎረቤት ሀገራት ልዩ ትኩረት ሰጠ? የሚያስገኘው ጥቅምስ ምን ያህል ነው? ስንል የተለያዩ ምሁራንን አነጋግረናል። የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአውሮፓና የአሜሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተንታኝ ዳር እስከዳር ታዬ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፣ በአብዛኛው በውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ከሀገራት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት በግልፅ ማስቀመጥ የተለመደ ነው። ግንኙነቱ የቅርብና የሩቅ ጎረቤት በሚል መከፋፈል ይቻላል።

በአመዛኙ ሀገራት በፖሊሲያቸው ለጎረቤት ሀገራት በተለያዩ ምክንያቶች ቅድሚያ ይሰጣሉ። አንደኛው ጂኦግራፊው ስለሚያስገድዳቸው ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከቅርብ ጎረቤት ጋር የሚኖረው የግንኙነት አድማስ በጣም ሰፊ መሆን ይችላል። ማለትም ከቅርብ ጎረቤት ጋር በሆነ ጥቂት ጉዳይ ብቻ እንገናኝ ማለት አይቻልም።

ለአብነት ኢትዮጵያ ከኤርትራ እና ከሶማሊያ ጋር የሚኖራት ግንኙነት እንደ ሌሎች ሀገራት በተመረጠ ጉዳይ ላይ ብቻ አይሆንም። ምክንያቱም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት አለ። የማንነት ተመሳሳይነት ይኖራል። ጎረቤት በመሆን ብቻ ሕጋዊና ሕገ ወጥ የንግድ ግንኙነት ይፈጠራል። ድንበር በጋራ ማስተዳደርም አለ። እንደ ዳርእስከዳር (ዶ/ር) ገለፃ፣ እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ሲታዩ ተወደደም ተጠላ ከጎረቤት ሀገር ጋር የሚኖረው ግንኙነት ጥብቅ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

ሌላው ዳርእስከዳር (ዶ/ር) የተብራራው፣ ከጎረቤት ሀገር ጋር ግንኙነት የሚመሠረተው በመምረጥ አይደለም። ጂኦግራፊው ራሱ አስገዳጅ ሁኔታን ይፈጥራል። ነገር ግን ከሌሎች ሀገራት ጋር ግንኙነት የሚመሠረተው በምርጫ ነው። ለአብነት ኢትዮጵያ እና ኢምሬት በጂኦግራፊያዊ አቀማመጣቸው ጎረቤት አይደሉም። ስለዚህ ግንኙነት ሊመሠርቱ የሚችሉት በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ከመካከለኛው አፍሪካ ሀገራት ከየትኞቹ ጋር መጠቃቀም እችላለሁ? ብላ መምረጥ ትችላለች። ያልፈለገችውን ሀገርም መተው መብቷ ነው።

ጎረቤት ሀገር ጋር ሲመጣ ግን፣ በዚህ መንገድ መምረጥ አይቻልም። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ፖሊሲ ከ2010 ወዲህ ለጎረቤት ሀገራት ትኩረት የሰጠ ሆኗል። ይህንን ተከትሎም በብዙ ሥራዎች ቅድሚያ ለጎረቤት ከመስጠት በተጨማሪ፣ ከሁሉም ጎረቤት ሀገራት ጋር መልካም ግንኙነት ለመመሥረት ጥረት ይደረጋል።

‹‹ከለውጡ አስቀድሞ በነበሩ ዓመታት በውጭ ጉዳይ ፖሊሲው ኤርትራን በጠላትነት የማቆየት ስትራቴጂ ነበር። ከሶማሊያና ከኬንያ ጋር የነበረው ግንኙነትም ሁልጊዜ ይህን ታሳቢ ያደረገ ነበር›› ያሉት የፖለቲካ ተንታኝ ዳርእስከዳር ታዬ (ዶ/ር)፣ አሁን ላይ ጎረቤት ተኮር እናድርገው ሲባል ግን፣ ሁሉንም ጎረቤት ሀገራት በተቻለ መጠን ወደ አንድ ማምጣት የሚያስችል ፖሊሲ ታስቦበት መዘጋጀቱን ተናግረዋል። በዋናነትም ከሁሉም ጋር በሰላም መኖርን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

ላለፉት ሃምሳ እና ስልሳ ዓመታት በአፍሪካ ቀንድ ላይ አንዱ በሌላ ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ይገባ ነበር። አንዱ የሌላ ሀገርን ተቃዋሚ ኃይል ከማሰልጠን በተጨማሪ የማስታጠቅና መሰል ልምዶች ነበሩ። ከዚህ የተነሳ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በኢትዮጵያና በጎረቤት ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት አንድ ጊዜ ሲሞቅ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቀዝቀዝ እያለ እንደየወቅቱ ሁኔታ የሚቀያየር ነበር። ለዚህ ዋነኛው ምክንያት አንዱ በአንዱ ጉዳይ ጣልቃ ይገባ ስለነበረ መሆኑን አስረድተዋል።



ዳርእስከዳር ታዬ (ዶ/ር)



ገመቹ አራርሶ (ዶ/ር)

**ላለፉት ሃምሳ እና ስልሳ ዓመታት በአፍሪካ ቀንድ ላይ አንዱ በሌላ ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ይገባ ነበር**

ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ለሁሉም የሚጠቅም ጎረቤት ተኮር ፖሊሲን ብታዘጋጅም፣ አንዳንድ ጎረቤቶች አሁንም ከኖሩበት ልማድ አለመላቀቃቸውን በመጠቆም፣ ቀላል ምሳሌ ብለው በቅርቡ የኤርትራው ፕሬዚዳንት በሰጡት ቃለ ምልልስ ብዙ ሰዓት ስለኢትዮጵያ ሲያወሩ ተደምጠዋል ብለዋል። እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ነበሩ፣ አሁንም አሉ። አሁን ላይ የተለወጠው ነገር ኢትዮጵያ በመፈቃቀድና በመተባበር ካልሆነ በስቀተር በጎረቤት ሀገር ጉዳይ እጇን አታስገባም። በዚህም ከጎረቤት ሀገራት ጋር ሰላማዊ ግንኙነት መፍጠር እና በኢኮኖሚ መተሳሰርን ዋነኛ ግቧ ሆኖ በመንቀሳቀስ ላይ እንደምትገኝ አመላክተዋል።

ጨምረውም ከዚህ በፊት ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለ ግንኙነት የሚቃኘው ከኃያላን ሀገራት ጋር ያለን ግንኙነት መሠረት በማድረግ እንደነበር አስታውሰው፣ አሁን ላይ ግን ይህ ተቀይሯል ብለዋል። ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለው ጥቅም የሚሰላው በራስ ውሳኔ መሆኑን አስታውቀው፣ ኃያላን ሀገራት ምን ይፈልጋሉ? ምን ይላሉ? የሚለውን መሠረት በማድረግ የቆመ መሆኑንም ተናግረዋል። ከዚህ አንጻር ለውጥ መኖሩንም አብራርተዋል።

በኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ለሶስት ዓመት ፕሬዚዳንት ሆነው ያገለገሉት እና በአሁኑ ወቅት በጨፌ ኦሮሚያ የምክር ቤት አባል እና የመንግሥት በጀት እና ሀብት አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ገመቹ አራርሶ (ዶ/ር) በበኩላቸው ዳርእስከዳር (ዶ/ር) ጋር ተመሳሳይ የሆነ ምልከታ አላቸው። እሳቸው እንደሚሉት ከዚህ በፊት የነበረው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አንዱን ሀገር ወዳጅ ሌላኛውን ደግሞ ጠላት ብሎ የሚፈርጅ ነበር።

ለአብነት ኤርትራን እንደ ጠላት የሚፈርጅ እንደነበር የገለፁት ገመቹ (ዶ/ር)፣ ከሶማሊያ ጋርም የነበረው ግንኙነት ጠንካራ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ላይ የተመሠረተ ትብብር እንዳልነበር ያስረዳሉ። የተወሰነ ከሌሎች የምዕራብ ሀገሮች ጋር በመሆን ሽብርተኝነትን የመዋጋት ሥራ ይሠራ እንደነበር አስታውሰው፣ ያም ቢሆን የነበረው ፖሊሲም ሆነ በተግባር ከጎረቤት ሀገራት ጋር የነበረው ግንኙነት ጤናማ አልነበረም ማለት ይቻላል ብለዋል።

ገመቹ (ዶ/ር)፣ መገለጫውም ብለው ያነሱት ከፖሊሲው ባሻገር በተግባርም ከኤርትራ ጋር በነበረው ግንኙነት ለሃያ ዓመታት ሰላምም ጦርነትም ውስጥ አልነበረም። ሁለቱ ሀገሮች አንዱ የአንዱን ስም ለማጠልሸት፣ አንዱ ሌላኛው ላይ የዓለም አቀፍ ጫና እንዲደረግበት ይሠራ ነበር። በጊዜው የነበረው ሥርዓትም ኤርትራ ላይ ጫና ለመፍጠር፣ ጤናማ ባልሆነ መልኩ ይንቀሳቀስ እንደነበር አስታውሰዋል።

አሁን ባለው በውጭ ጉዳይ ፖሊሲም ሆነ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ባለው ግንኙነት የቆየውን የፖለቲካ ዕሳቤ በመቀየር፣ ጠላት ብሎ መፈረጅ ቀርቷል ብለዋል። ከሀገሮች ጋር የሚኖረው ግንኙነት በተለይም ከጎረቤት ሀገሮች ጋር፣ በዋናነት የጎረቤት ሀገሮች ሲባል ኤርትራን ጨምሮ የሚኖረው ግንኙነት ትልልቆቹ ጉዳዮች ብሔራዊ ጥቅም እና የዜጎች ክብር መሠረት ባደረገ መልኩ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ ገመቹ (ዶ/ር) ገለፃ፣ ከለውጡ ወዲህ በተግባርም በመካከላቸው ጦርነትም ሰላምም ያልነበረባቸው ኢትዮጵያ እና ኤርትራ እርስ በእርስ እንዲቀራረቡ ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ናቸው። በዚህም የኖቤል ሽልማት እስከ ማግኘት ደርሰዋል። አሁን በተግባርም እየተሠራ ያለው ይኸው ነው። አሁንም የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራ ጠላቴ ናት ብሎ አልፈረጀም። አሁንም የሚታመነው የኤርትራ ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወንድም እንደሆነ ነው።

የኢትዮጵያ አዝማሚያ አብሮ የመልማት እና የማደግ፣ በጋራ የቀጣናውን ሰላም የማስከበር ነው። ይህ ከየትኛውም ጎረቤት ሀገር ጋር በሚኖረው ግንኙነት የሚታይ መሆኑን ጠቁመው፣ በተቃራኒው ግን በሕዝብ ደረጃ ሳይሆን መንግሥታት ወይም ሥልጣን ላይ ያሉ አመራሮች አልያም በዛ ሀገር ያለው ሥርዓት ቀና የሆነ ግንኙነት ላይኖረው እንደሚችል ጠቁመዋል። ይህ ሲሆን ግንኙነቱ በተመሳሳይ መልኩ ትርጉም ላይሰጠው ይችላል ብለዋል።

ለዚህ የራሱ ምክንያት ሊኖረው ይችላል ያሉት ገመቹ (ዶ/ር)፣ ምናልባትም አንዳንዴ የኃይል ግፊያ ግንኙነትን እንደሚያሻክር አብራርተዋል። ይህች ሀገር በኢኮኖሚ ከተጠናከረች ተፅዕኖ ልትፈጥር ትችላለች የሚል ግፊያ ይኖራል። በግለሰብ ደረጃ ሽፍጥ ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ከጎረቤት ሀገር ተመሳሳይ ምላሽ ላይኖር እንደሚችል አመላክተዋል።

በኢትዮጵያ በኩል የጎረቤት ሀገር ምላሽ ምንም ሆነ ምን ኢትዮጵያ ግንኙነቷ ሰላማዊ እንዲሆን ፍላጎቷን በመግለጽ ላይ እንደምትገኝ ጠቁመው፣ ይህ ደግሞ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አብራርተዋል። ያልተረጋጋች ሶማሊያ፣ ኤርትራ ወይም ኬንያ ቢኖሩ ኢትዮጵያ ምንም ልታተርፍ አትችልም። እንደውም እነርሱ ሰላም ካልሆኑ ኢትዮጵያም ሰላም መሆን አትችልም። ሰላም ካልሆነች ደግሞ ትኩረቷን ልማት ላይ ለማድረግ እንደምትቸገር አስረድተዋል።

ሌላው የቀጣናውን ኢኮኖሚ ማስተሳሰር ቢቻል ቀጣናው በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ይሆናል። ምክንያቱም ኢትዮጵያ የምታንቀሳቅሰው ትልቅ ኢኮኖሚ ነው። ኬንያም የምታንቀሳቅሰው ኢኮኖሚ ትልቅ ነው። ሁሉም ሀገሮች የራሳቸው ፀጋ አላቸው። ይህንን ፀጋቸውን ማቀናጀት ቢቻሉ፣ እያንዳንዱ ሀገር በተለያየ መልኩ ተጠቃሚ ይሆናል። በቀጣናውም በጣም ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት ይቻላል ብለዋል።

ለሁሉም ነገር መሠረቱ ኢኮኖሚ ነው። ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት ከተቻለ፣ ጠንካራ ደህንነት ይኖራል። የቀጣናው ተሰሚነት ይጨምራል። ያሉት ገመቹ (ዶ/ር)፣ ይህ ሲሆን ማንም እንደፈለገው እጅ መጠምዘዝ የሚችልበት ዕድል ይዘጋል። በደህንነት ጉዳይ ላይ መተሳሰርም ከባድ እንደማይሆን አስረድተዋል።

ሌላው በገመቹ (ዶ/ር) የተነሳው፣ ቀይ ባህር የአፍሪካ፣ የአውሮፓ እና የኤዢያ አህጉራት በንግድ የሚተሳሰሩበት ነው። ቀጣናው በጣም ስትራቴጂክ ነው። በጣም ትልቅ የዓለም ኢኮኖሚ የሚንቀሳቀስበት ቀጣና በመሆኑ፣ በርካታ ሀገራት ምስራቅ አውሮፓዎች ሳይቀሩ የጦር ሠፈር (ሚሊተሪ ቤዝ) ይዘዋል የሚለው ነው።

ይህ ማለት ቀጣናው ላይ በጣም ስትራቴጂክ ጥቅም አለ። ስለዚህ የቀጣናው ሀገራት በጋራ በመሆን፣ ከዚህ አካባቢ የሚገባቸውን ድርሻ ማግኘት አለባቸው ብለዋል። የሩቅ ሀገር መጥቶ ፍላጎት እያሳየ ኢትዮጵያ ችላ ብላ ልትቀመጥ አትችልም። ስለሆነም በቅርብ ያሉ ሀገራት እርስ በእርስ ከመገፋፋት ይልቅ ተባብረው በአንድነት ከተንቀሳቀሱ በቀጣናው ላይ ማሳደር የሚገባቸውን ጫና ማሳደር ይችላሉ የሚል እምነት እንደላቸውም ተናግረዋል።

እንደ ገመቹ (ዶ/ር) ገለፃ፣ ተባብረው በአንድነት መቆማቸው ተፅዕኖ መፍጠር ባይችሉ እንኳ ቢያንስ የሚመጣባቸውን አሉታዊ ጫና መመለስ የሚችሉትን ዕድል መፍጠር ይችላሉ። ለዚህም እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ የጎረቤት ሀገራትም ፖሊሲያቸውን ጎረቤት ተኮር አድርገው ሰላማዊ ግንኙነት ላይ እና የጋራ ጥቅምን በማስከበር ዙሪያ መረባረብ ይገባቸዋል።

የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ግን ከሶሻሊስት እና ከካፒታሊስት ሀገራት ጋር፣ ከምዕራባውያን እና ከምስራቅ ሀገራት ጋር እያለ ይከፋፍል ነበር። ለቀጣናው ሀገራት ለአብዛኞቹ ትኩረት የሚሰጥ ፖሊሲ አልነበረም። አሁን ግን ኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የጎረቤት ሀገር ላይ ትኩረት አድርጎ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን፣ የደህንነት እና የማህበራዊ ትስስርን እንዲሁም የሕዝቦችን ታሪካዊ ትስስር ላይ ተመስርቶ እየተሠራበት ይገኛል። ይህም በፅኑ የሚደገፍ መሆኑን አመላክተዋል።

እንደ ምሁራኑ ገለፃ፣ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው ላይ እንደተቀመጠው ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖሩት ግንኙነቶች የሀገሪቷን ብሔራዊ ጥቅም መሠረት ባደረገ እና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ነው። የሀገራትን ሉዓላዊነት እና ፍላጎታቸውን በማይነካ መልኩ የዜጎቻችንን ክብርም በጠበቀ ሁኔታ የተቀረጸ በመሆኑ አዋጭነቱ አጠራጣሪ አይደለም።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ከጠንካራ እጆች በስተጀርባ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የሕይወትን ክፉ እና ደግ ገጽታዎች በአረቦቹ ምድር ኖራ አይታዋለች፤ ለድፍን አስር ዓመታት። አጋጣሚዎች ምንም ይሁኑ ምን ለእሷ የለውጥ ርምጃዎች ናቸው። ሁሌም ጥንካሬን ከብርታት ደርባ ለመነሳት ምክንያት ይሆኗታል። ምንጊዜም ሃሳብን ወጥኖ፣ በሥራ መተግበርና ለሌሎች ጭምር ሥራ መፍጠር ብርቋ አይደለም ወይዘሮ መቅደስ ውብነህ።

ከዓመታት በፊት እሷና ጥቂት ጓደኞቿ ብዙ የማይባል የመነሻ ካፒታል ይዘው በጋራ ለመሥራት ተደራጁ። ያኔ «ጉድሼፐርድ» የተባለ ግብረሠናይ ድርጅት አጋር ሊሆናቸው ከጎናቸው ቆመ። በወቅቱ ሥልጠናን ጨምሮ ለሥራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችና የመቋቋሚያ ገንዘብ ከእጃቸው አላጡም። ውሎ አድሮ የራሳቸውን ሥራ ለመጀመር አቅም አገኙ። መደራጀታቸው ኃይል ሆኖም ትጋታቸው በተግባር ይገለጽ ያዘ።

እነመቅደስ በአዲሱ ገበያና አካባቢው ቦታ አግኝተው ሥራ ሲጀምሩ በቁጥር አስራ አምስት ነበሩ። ብርቱዎቹ ነገን የተሻለ ለማድረግ ጠንከረው መሥራት ጀመሩ። የመጀመሪያው የጥረታቸው ሀሁ የታየው ዳቦ ጋግሮ መሸጥ ላይ ነበር። አጋጣሚ ሆኖ ከሥራው መጀመር ጋር እክል አላጣቸውም። ዳቦውን ለመጋገር የተሰጣቸው የመብራት ኃይል መጠን ዝቅተኛ መሆን አቅማቸውን ያንገዳግደው ያዘ። እንዲያም ሆኖ እጅ አልሰጡም። በቻሉት አቅም ከነሱ ሳያጎድሉ ሌት ተቀን ባተሉ። ያለው የመብራት አቅም የዳቦ ማሽኑንና ማቡኪያውን ማንቀሳቀስ አልቻለም። እንዲህ መሆኑ በግለት የጀመሩትን ሥራ ማቀዛቀዙ አልቀረም። ውሎው አድካሚ ቢሆንም ትግላቸው ያለ እረፍት ቀጠለ። ጥቂት ለማይባል ጊዜ ሁሉም ሥራውን ለማሸነፍ ጣረ፣ ደከመ።

ውሎ አድሮ ግን «ሰለቸን ፣ደከመን» ያሉቱ ከቡድኑ ተንጠባጠቡ። አብዛኞቹ በሚሆነው ሁሉ ተስፋ ቆርጠው ነበር። የተቀሩት ጥቂቶች ላባቸውን ጠርገው፣ ትከሻቸውን አጉብጠው ወደሥራው ተመለሱ። አሁንም ትግሉ አልቆመም። መቅደስና ጥቂት ባልንጀሮቿ ከዓላማቸው አልሳቱም። አድካሚውን ውሎ ለማቃናት ደፉ ቀናቸውን ተያያዙት።

መቅደስ ፈጽሞ ክንዷ አልዛለም። እንደሷ የበረቱትን ይዛ ከሥራው ላይ ዋለች። ድካሟ ውሉን አልሳተም። የጠፋውን እያረመች፣ የጎደለውን እየሞላች በጽናት መጓዟን ቀጠለች። ይህ ትግል ካሰበችው ሊያደርሳት አልዘገየም። በበቂ የኤሌክትሪክ ኃይል የዳቦ ማሽኑን ተክላ፣ ማቡኪያውና ማኮፈሻውን አቁማ ሥራውን በአዲስ መልክ ጀመረችው።

የመቅደስ ተጨማሪ ሌላ ሥራም ወጠነች፤ እንጀራ እያስጋገረች ማከፋፈሉን ቀጠለች። ይህ አጋጣሚ ደግሞ ለብዙዎቹ መልካም ሆኖ ሥራ የመፍጠር ዕድሉን አሰፋ። አስር ሠራተኞች ቋሚ የደሞዝ ተከፋይ ሆነው መተዳደሪያቸውን አገኙ። በእንጀራው ዝግጅቱ ሌሎችም እንጀራ ወጣላቸው።

ሥራ ባለ ጊዜ እየተገኙ ጎዶሏቸውን አሟሉ። በየቀኑ ትኩስ እንጀራ በተፈለገበት ቦታ በጊዜው መድረስ፣ መከፋፈሉን ቀጠለ። መቅደስና አጋሮቿ ሥራው በዚህ ብቻ «ይብቃን» አላሉም። የእጅ ሙያቸውን የሚያስመሰክሩበትን ዕድል አስፋፉ። ሙሉ የባልትና ውጤቶች፣ ቡላና ቆሎ፣ ቅመማ ቅመሞች መታወቂያቸው ሆነ። ባዘርና መሰል ዝግጅቶች በኖሩ ጊዜ ፈላጊ ደንበኞቻቸው በረከቱ።

ምርቶቻቸው ከተለመደው ሽያጭ ተሻግረው በመርካቶ ሱቆች ማከፋፈላቸው ደግሞ እውቅናን ማስደሩ አልቀረም። በአውቶቡስ ተራና አካባቢው አሁንም ድረስ የእነሱ ቆሎ ተመራጭ ሆኗል። መቅደስ መቼም ቢሆን ይህን ጅማሬ ባለበት ማቆም አትሻም። ከተለያዩ ክልሎች የምታስመጣቸውን ምርቶች ወደ ውጭ ሀገራት የመላክ ህልምን ሰንቃለች።

እንደ ወይዘሮዋ አባባል የቡላ ምርትን የምታስመጣው በአብዛኛው ከደቡብ የሀገራችን ክፍል ነው። ምርቱ ተፈላጊና ተመራጭ በመሆኑ ማስተዋወቅና አስፋፍቶ መሸጥ የወደፊት ዕቅዷ ነው። የተለያዩ የማር ዓይነቶችን በአግባቡ በማስገባትም በተለያየ የኪሎ መጠን አሽጋ ትሸጣለች። የምታስመጣቸው የማር ምርቶች መገኛቸው ይለያያል። እንዲህ መሆኑ ሽያጩን በዓይነት፣ በጥራትና በፍላጎት ለይቶ ለማቅረብ አስችሏታል።



ወይዘሮ አሰለፈች አለዶ፤

መቅደስ አብረዋት ሥራውን የጀመሩ ባልንጀሮቿ በተለያዩ ምክንያቶች ዛሬን ከእሷ ጋር አይደሉም። የእነሱ መለየት ሳይበግራት የቀጠለችው ሥራ ግን አሁን ከራሷ አልፎ ለሌሎች እየተረፈ ነው። አስቀድሞ ስያሜ ያወጡለት የ«ኪነጥበብ፣ መቅደስና ጓደኞቻቸው ህብረት ሥራ በብዙ ፈተናዎች ቢመላለስም ተደናቅፎ አልወደቀም። ዳግም አርማውን ባነሳችው መቅደስ የበረታ ክንድ እስትንፋሱ ቀጥሏል። መገኛዋን አዲሱ ገበያ ዙሪያ ያደረገችው ወይዘሮ የነገው ትጋቷ ሁሌም የሰላ ነው። ትናንትን በዋለችበት መስመር ዛሬን እየበረታች ትጓዛለች።


በየቀኑ እየተጋገረ ለገበያ በሚከፋፈለው እንጀራ ጥራት ጉዳይ አትደራደርም። ከምንም በላይ በንጽህናና በታማኝነት ማዘጋጀት የህሊና እረፍት መሆኑን ትናገራለች። እንጀራው በዋነኛነት ለውጭ ተጠቃሚዎች ተዘጋጅቶ ይቅረብ እንጂ ለራሳቸውም ጭምር የሚመገቡት ነው። በየጊዜው ከሚመለከታቸው አካላት ተገቢው ክትትልና የጥራት ቁጥጥር ይደረግበታል።

ከመንግሥት በተሰጣቸው ስልሳ ካሬ የማምረቻ ቦታ ላይ ተገቢው ተግባራት መከወን ይችል ዘንድ ጊዜና ጉልበት በወጉ ተቀናጅተዋል። በዚህ ሥፍራ ለሰው ልጆች ምግብ የሚሆነው የዕለት እንጀራ በንጽህና ይጋገራል። ዳቦና ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶችም በትኩሱ ተዘጋጅተው በየቦታው ይደርሳሉ።

የአካባቢው ሱቆች፣ አነስተኛ ምግብ ቤቶች፣ ካፌዎችና ዳቦ ቤቶች የነመቅደስን የጓዳ ሙያዎች ለመቀበል የሚዘጋጁት ገና ከማለዳው ነው። የዕለቱ ፍላጎት ተጠናቆ የነገውን ለማቅረብ ትዕዛዝ የሚቀበሉት እጆች ፈጣንና እረፍት አልባ ናቸው። ሁሌም በሥራ ውለውና አምሽተው ከነገ ለመድረስ ስንፍና ይሉትን አያውቁም።

ብርቱዋ ወይዘሮ ከዓመታት በፊት ባለቤቷን በሞት አጥታለች። እንዲህ መሆኑ ሀዘኗን ቢያከፋውም ተሰብሮ ለመውደቅ አልተመቸችም። ዛሬም ሁለት ልጆቿን በጥንካሬ እያሳደገች ነው። አንደኛው ልጇ አያቶቹ ዘንድ እየኖረ ቢሆንም ሁለተኛ ዲግሪውን እየተማረ ይገኛል።

ሁለተኛዋ ልጇ ዛሬ የአስራ ስድስት ዓመት ታዳጊ ነች። ከእሷ ጋር አብራት እየኖረች ትማራለች። የልጇን ጉብዝና ደጋግማ የምታውሳው መቅደስ የእሷ ጥንካሬ እንደተጋባባት የምትናገረው በርግጠኝነት ነው። ልጆቿ ያለ አባት ቢያድጉም በጎዶሎ ስሜት እንዲቀጥሉ አትሻምና ስለትምህርታቸው አብዝታ ታስባለች። በቤትም ይሁን በውጭ የእናት አባትን ኃላፊነት መሸከም የእሷ ድርሻ ቢሆንም ስለእነሱ ዝም አትልም።



ወይዘሮ መቅደስ ውብነህ፡

ከጠንካራ እጆች በስተጀርባ የበረቱ ሁሌም ሥራቸው በጥንካሬ ይገለጻል። ማንነታቸው በትጋት ጠንክሮም ሕይወታቸው በገሀድ ይመሰክራል። እንዲህ ዓይነት እጆች ያላቸው ብርቱዎች በሻካራው መዳፋቸው ነጋቸውን አሳምረው ይገነባሉ። በጥረታቸው፣ በላባቸው በረከት ብሩህ ተስፋን ያፈካሉ። ሁሌም በዚህ ዓይነት መንገድ የሚራመዱ በጉዞ አይደክሙም። ከራሳቸው አልፈው፣ ለቤተሰቦቻቸው መድህን ሊሆኑ ይቻላቸዋል።

እናት መቅደስ ስለ ልጆቿ ብዙ ታልማለች። ሁሌም የእሷን ፈለግ ተከትለው ከዓላማዋ እንዲደርሱ ምኞቷ ነው። አሁን ያሉበትን ጅማሬ ስትገመግመው ግን ልጆቿ ከእሷ ልቀዋት እንደሚያልፉ ትገምታለች። እሷ ዛሬ ላይ በልማዳዊ አሠራር የጀመረችውን መስመር እነሱ ወደፊት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንደሚተኩት ስትናገር ያለ አንዳች ጥርጣሬ ነው። ብርቱዋ ወይዘሮ መቅደስ ውብነህ።

ወይዘሮ አሰለፈች አለዶ በተለያዩ የሥራ ፈጠራዎች በሥልጠና ስትሳተፍ ቆይታለች። ለእሷ ውስጠት ቀርቦ ያገኘችው ሙያ ግን የልብስ ስፌትና የሀገር ባሕል ልብሶች ሽያጭን ነው። በዚህ ሙያ የተለያዩ አልባሳትን ሰፍታ በማዘጋጀት ለጠየቋት ደንበኞቿ በመሸጥ ትተዳደራለች።

አሰለፈችን ያገኘኋት በቅርቡ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በነበረው ዓለም አቀፉ የኢንተርፕሪነርሺፕ ሳምንት ላይ ነበር። እሷም ልክ እንደነመቅደስ ሁሉ የራሷን የሥራ ውጤቶች ለእይታ አቅርባ ለሽያጭ አውላለች።

አሰለፈች ሰፍታ የምታዘጋጀቻውን የሀገር ባሕል ልብሶች ከደንበኞቿ ባለፈ በብዛት ለሚፈልጉ ነጋዴዎች ጭምር ታስረክባለች። የእጇን ሙያ የሚያውቁ አንዳንዶች በፍላጎታቸው መጠን እንድትሠራላቸው ይሻሉ። ትዕዛዛቸውን ተቀብላ የልባቸውን ትሞላለች።

አንዳንዴ የሠራቻቸውን የሀገር ባሕል ልብሶች ባዛር ላይ ተገኝታ ትሸጣለች። አሁን እንደተገኘችበት የኢንተርፕሪነርሺፕ ዓይነት ቆይታ ሲኖራት ደግሞ ምርቶቿን በማሳየት ከብዙሃን ጋር መተዋወቅን ልምድ አድርጋለች። አሰለፈች ጥሬ ዕቃዎችን ገዝታ ከባሕላዊው ጋር ማዛመዷ ልብሶቹ ማራኪ እንዲሆኑላት ምክንያት ሆኗል። ይህ እውነታም ተፈላጊነትን አስከትሎ ለገበያው መወደድ አግዟታል።

በአሰለፍ ገበያ ውስጥ የሸማኔ ሥራና የፋብሪካ ውጤቶች የተዛመዱ ናቸው። ጥለትና ጥበቦች በግል ፈጠራዋ ተውበው ከዘመናዊ አልባሳት ተዛምደው ይቀርባሉ። የህጻናትና የአዋቂዎች አልባሳት በተለያየ ዲዛይን መዘጋጀታቸው ለገዢዎች ምርጫና ልዩነትን ለመፍጠር ምክንያቶች ናቸው።

አሰለፈች ይህን መሰል ክህሎት ለማዳበር በሙያው የወሰደችው ሥልጠና አግዟታል። በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ተደራጅታ በርካታ ዕውቀት አዳብራለች። ከሥልጠናው በኋላ ለአምስት ዓመታት የመሥሪያና መሸጫ ቦታ አግኝታ ምርቶቿን ለገበያ ስታቀርብ ነበር። ከነዚህ ዓመታት በኋላ ወደ ተገቢው ደረጃ በማለፏ ራሷን ችላ እንድትቀጥል አስችሏታል።

መኖሪያዋን ኮዬ ፈጬ ላይ ያደረገችው አሰለፈች ባለችበት ስፍራ ገበያውን ለማላመድ እየጣረች ነው። ከማህበር ሥራ ተነጥሎ ወደግል ሲመለሱ መንገዶች አልጋ በአልጋ አይሆኑም። የመሥሪያ ቦታ፣ የማቴሪያል አቅርቦትና ሌሎችም ግብዓቶች ያስፈልጋሉ። ወይዘሮዋ በቆይታዋ ያዳበረችው ልምድ ለዚህ አጋጣሚ ሲያግዛት ቆይቷል። ያላትን አቅም ላሰበችው ዓላማ ባዋለች ጊዜ አልተቸገረችም።

በአካባቢው አልባሳቶቹን አዘጋጅታ ለመሸጥ የሚያስችላትን ሱቅ ተከራየች። አቅርቦቶቹን አይተው የወደዱላት በርካቶች ደንበኞቿ ሆኑ። ለአዘቦት ቀንና ለዓውደ ዓመት ሱቋን መጎብኘት ልምዳቸው ሆነ።

ወይዘሮዋ የባዛር አጋጣሚዎችን በምታገኝ ጊዜ ዕድሉን ትጠቀማለች። በዓይነትና በብዛት የምታቀርባቸው አልባሳት ገበያ ለመሳብ አይዘገዩም። ባሕላዊ አልባሳቱ አውደ ዓመት በደረሰ ጊዜ ፈላጊያቸው ብዙ ነው። እሷም እንደየጊዜው ፍላጎት አመቻችታ ማዘጋጀት ይጠበቅባታል።

አሰለፈች ገበያው ቀዝቀዝ ሲልባት ጊዜዋን የምትጠቀመው ምርቶችን በማዘጋጀትና ትዕዛዞችን በመቀበል ነው። ሥራው ላይ በዋለች ጊዜ መሰልቸት ይሉትን አታውቅም። ሙያው በራሱ ያሳደረባት ፍቅር ዕለት በዕለት እንድትገኝበት ምክንያት ሆኗል።

አንዳንዴ አሰለፈች በሥራው ላይ የምትፈተንበት አጋጣሚ አይጠፋም። የመኖሪያ ሰፈሯና የጥሬ ዕቃው መገኛ መራራቁ የምትሻውን ፈጥኖ ለማግኘት ያስቸግራታል። መርካቶ ከምትኖርበት የኮዬ ፈጬ አካባቢ በኪሎ ሜትሮች የራቀ ነው። ለሀገር ባሕል አልባሳቱ ጥልፍ የሚሰሩላት ባለሙያዎችም በአቅራቢያዋ የሉም። ይህ እውነት በተለይ በአውደ ዓመት አካባቢ ቀላል የማይባል የድካም ዋጋ ያስከፍላታል።

ወይዘሮዋ ባለትዳርና የልጆች እናት ነች። ታላቅ ኃላፊነት አለባትና ጊዜዋን ለውጭ ሥራ ብቻ አታውልም። ቤተሰብ ማስተዳደር፣ ቤትን መምራትና ጓዳን መሙላት ይጠበቅባታል። የውጭውን ከቤቱ አቻችላ ለማሳደር እጆቿ ሁሌም ብርቱ ናቸው። በየጊዜው በጥንካሬ ሰልተው ይውላሉ።

አሰለፈች ከጊዜ ወደጊዜ የባሕል አልባሳትን የሚመርጡ ሰዎች ቁጥር መበራከቱን አስተውላለች። የተጠቃሚው ፍላጎት መጨመርም ለእሷ መሰል ባለሙያዎች ዕድል እንደሚፈጥር አታጣውም። ክንዶቿ ሳይዝሉ የመትጋቷ አንዱ ሚስጥርም ይኸው ነው። በተለይ በዓውደ ዓመት ጊዜ የእጇ አቅርቦት እስኪያንሳት የምትቸገርበት አጋጣሚ ይኖራል።

ወይዘሮዋ የምትኖርበትን አካባቢ የአልባሳት ፍላጎት ለይታለች። እንደ ደንበኞቿ ጥያቄም በተለያዩ ጨርቆች የራሷን ዲዛይን አዘጋጅታ ለገበያ ታውላለች። አሰለፈች በጀመረችው መንገድ ጠንክራ የመግፋት ዕቅድ አላት። ነገን የተሻለ ለማድረግም የዛሬ እርሾዋ በወጉ መዘጋጀት ይኖርበታል።

ይህን ጠንቅቃ የምታውቀው ብርቱ ወደፊት ተጨማሪ ሱቆች የማከል ዓላማን ወጥናለች። ለዚህ ደግሞ በተሻለ አቅርቦትና በዘመናዊ አሠራር ጊዜዋን መጠቀም ግድ እንደሚል ገብቷታል። አሰለፈች ዛሬ ላይ ቆማ ነገን በመልካም እያለመች ነው። ህልሟ ዕውን ይሆን ዘንድ ጠንካራ እጆቿ በአእምሮዋ ታግዘው መትጋታቸውን ቀጥለዋል።

ሁለቱ ብርቱ ሴቶች ከትናንት መነሻቸው ተንደርድረው ዛሬን የተሻለ ለማድረግ እየጣሩ ነው። በግልጽ ከሚታየው ውጤታማ ተግባራቸው ጀርባ ጠንክረው የሚሠሩ እጆቻቸው ድካምን አያውቁም።

እነዚህ እጆች ዛሬ ለተገኙበት ውጤታማ ዓለም መሠረት ሆነው አበርትተዋቸዋል። ነገ ለሚጓዙበት የዕድገት ጎዳናም ምስክር ሆነው ይቀጥላሉ። ከጠንካራ እጆቻቸው በስተጀርባ ታይቶ የሚረጋገጥ፣ ውጤታማ ፍሬ ጎምርቷልና።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ዛሬ ላይ ሆነን የኢትዮጵያን ትናንት ማወቅ ከፈለግን የትም መሄድ አይጠበቅብንም፣ ምስሏ አዲስ ዘመን ላይ እናገኘዋለን፡፡ ረሃብና ጠኔ፣ ችግርና እጅ ማየት ሳይሆን እጅ ነስተው ከእጇ ላይ የጎረሱ ሀገራት ብዙ ነበሩ፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ለእንግሊዝ ርዳታ ሰጥታ ነበር ቢባል ማናችን እናምናለን...አዲስ ዘመን ግን ከነደብዳቤው አስረግጦ ያስታውሰናል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ ቤቶች በሙሉ አንድ ዓይነት ትዕዛዝ፣ አንድ ዓይነት ቀለም እንዲቀቡ ተወስኗል፡፡ 250 ዓመታት ዕድሜ የነበረው መስቀል ከሀገር ሲወጣ ሲል... እንዲሁም የሥራ ፈቶቹን ጉዳይ የሚያጠና ኮሚቴም ተቋቁሟልና ሌሎች ወንጀል ነክ የጋዜጣውን ዘገባዎችንም ለዛሬ እናስታውስ።

### ኢትዮጵያ እንግሊዝን ረዳች

...

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በክረምቱ ኃይለኛነት ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት ሀገር የገንዘብ ርዳታ ልከዋል። ይህም ርዳታ በሌጋሲዮናችን በኩል ሲላክ ቀጥሎ ያለው ደብዳቤ አብሮ ተልኳል፡፡

### ለሎርድ ሜዮርክ ናሽናል ዲስትሪክት ፈንድ ለንደን

...

"ምንም እንኳን እኛም ራሳችን በሕዝባችን ላይ ያለአግባብ የደረሰበትን ጉዳት በማቃለል ሥራችን ላይ ብንሆንም ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቀው ኃይለኛና ጨካኝ በሆነው ክረምት ሁልጊዜ በምናስባት በለምለሟ ውብ በሆነች ሀገርዎ ላይ ለደረሰው ጥፋት መጠነኛ የገንዘብ ርዳታ መጠየቅዎን ስለሰማን የገንዘቡ ቁጥር ምንም ከፍ ያለ ባይሆን የኛንና የሕዝባችንን ርዳታ ለመግለጽ ያህል አንድ ሺህ ፓውንድ በሌጋሲዮናችን በኩል ልከንልዎታል፡፡"

**(አዲስ ዘመን መስከረም 23 ቀን 1940ዓ.ም)**

...

### በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት ቤቶች ተመሳሳይ ቀለም እንዲቀቡ ትዕዛዝ ተሳለፈ

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድና የሌላም ዓይነት ተግባር ማከናወኛ መደብሮች ከዚህ ወር ጀምሮ ለአካባቢው የሚስማማ ቀለም እንዲቀቡ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል። ይህን ማሳሰቢያ የሰጡት ክቡር ሚኒስትር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ፣ የአዲስ አበባ ከንቲባ ናቸው።

የሚቀቡትም ቀለም አልባሌ ሳይሆን በዓይነቱና በጥራቱ የተሻለ መሆን አለበት። የቀለሙንም ዓይነት በየክፍሉ የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች ሊሰጡ ይችላሉ ሲል የማዘጋጃ ቤቱ የማስታወቂያና የሕዝብ ኅብረት ማስፋፊያ ክፍል በተለይ ለአዲስ ዘመን ገልጧል።

የአዲስ አበባ ከተማ በአየርና በከፍተኛ ሥፍራ ሆነው ሲያዩት አብዛኛውን ቤት ጣራው የቆሸሸ፤ ቀለሙ የዛገ ሆኖ ይታያል። ስለዚህ እንደ ባለቤቱ መራጭነት አረንጓዴ ወይም በቀይ ቡናማ ቀለም መቀባት አለበት የሚል ማሳሰቢያ ክቡር ከንቲባው መልዕክት ውስጥ ይገኛል። ያረጀውም ጣሪያ እንዲለወጥ የክፍሉ ባለሥልጣኖች በጥብቅ ታዝዘዋል።

**(አዲስ ዘመን፣ መስከረም 7 ቀን 1964 ዓ.ም)**

### የሥራ ፈቶችን ጉዳይ የሚያጠና ኮሚቴ ተቋቋመ

የሥራ ፈቶችንና ትምህርታቸውን እያቋረጡ የሚወጡትን ልጆች የወደፊት ዕድል የሚወስን "ኦፖርቹኒቲዝ ኢንዱስትራላይዜሽን ሴንተር" የተባለ ድርጅት በኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ማቋቋሙን የድርጅቱ መሪ ዶክተር ሊአን ኤች ሱሊቫን ትናንት አስታወቁ። የድርጅቱ ዋና ዓላማ የሰው ልጅ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትንና ከጤናማው ህብረተሰብ የማይለይበትን መንገድ በመፈለግ የአዕምሮና የተግባር እውቀት ሰጥቶ ሥራ ለማስያዝ መሆኑ ተረጋግጧል።

የሥራ ፈቶችና ትምህርት የሚያቋርጡ ልጆች ማሰልጠኛና መደገፊያ ድርጅት ከአፍሪካ መሬት በናይጄሪያና በጋና ሥራ መጀመሩ ታውቋል።

...

**( አዲስ ዘመን ግንቦት 25 ቀን 1963 ዓ.ም)**

### ሁለት መቶ ሃምሳ ዓመት ዕድሜ ያላቸው መስቀሎች ወደውጪ ሲወጡ ተያዙ

በግምት ሁለት መቶ ሃምሳ ዕድሜ ያላቸውን ሁለት የእንጨት መስቀሎች አንድ የውጪ አገር ዜጋ ገዝተው ወደ ሀገራቸው ለመውሰድ ሲዘጋጁ መስቀሎቹ ተይዘው እዚሁ እንዲቀሩ መድረጉን ከብሔራዊ ሙዚየም የተገኘው ዜና አስታወቀ፡፡

መስቀሎቹን እዚሁ ለማስቀረት የተቻለው ከአዲስ ከተማ በገንዘብ የገዟቸው አንድ የውጪ ሀገር ዜጋ ወደ ብሔራዊ ሙዚየም ሔደው ወደ ውጪ ለማውጣት የሚያስችል ፈቃድ በጠየቁበት ወቅት መሆኑ ተገልጧል።

....

የተጠቀሱት የውጪ ሀገር ተወላጅ መስቀሎቹን ከየት እንደገዙ ተጠይቀው የገዙበትን ቦታ አሳይተዋል። በዚሁ መሠረት የሸጠው ሰው እንዲያዝ ተደርጎ ወደ አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ መወሰዱንና መስቀሎቹም በጣቢያው እንደሚገኙ ዜናው አስረድቷል፡፡

**(አዲስ ዘመን ታህሳስ 13 ቀን 1964ዓ.ም)**

...

### በጋቢ እየሸፈኑ የሚቀሙ ለፍርድ ቀረቡ

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከመሃል አራዳ ተላላፊ መንገደኞችን በራሳቸው ጋቢ እያከናነቡ ገንዘብና ልዩ ልዩ ዕቃዎች የሚቀሙት በፖሊስ ተይዘው ለፍርድ ቀረቡ፡፡

ተከሳሾቹ ኃይሉ አሸናፊና ጌታቸው ኃይሌ የተባሉት ወንጀሉን ፈጽመዋል በመባል የተያዙት አዲስ አበባ ደጎል ዓደባባይ አጠገብ መሆኑን ከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበባቸው የዓቃቤ ሕግ ክስ ይዘረዝራል። ወንጀሉ ተፈጽሞበታል የተባለው አቶ ጫኔ አበበ የተባለው ሰላማዊ ሰው ሲሆን፤ ተከሳሾቹ የግል ተበዳዩን በጋቢ አፍነው የነጠቁት ኅዳር 4 ቀን 1965ዓ.ም ከምሽቱ 3 ሰዓት ላይ መሆኑ ተገልጧል፡፡

...

**(አዲስ ዘመን ህዳር 10 ቀን 1965ዓ.ም)**

### የሕዝብ ማመላለሻ ወይንስ የእንጨት?

የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች በተለይ የከተማዎቹ የሕዝብ እንጂ የእንጨት ማመላለሻ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ይሁንና በአዲስ አበባ ከተማ በ6/12/1979 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰዓት ላይ የሠሌዳ ቁጥር 12192አ-አ በሆነ በ30 ቁጥር አውቶብስ ሲሠራ በዋለ አውቶብስ ላይ፣ አውቶብስ ተራ ላይ እንጨት ተጭኖበት አንድ መኖሪያ ቤት ደርሶ ሲራገፍ አይቼ ሁኔታው ገርሞኛል፡፡ ...ታዲያ የሕዝብ ወይንስ የእንጨት ማመላለሻ?

**(አዲስ ዘመን መስከረም 12 ቀን 1980ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## በነጻ ምግብ ዕደላ ላይ በተከሰተ ግፊያና መረጋገጥ 22 ሰዎች ሞቱ

በናይጄሪያ ደቡባዊ ምስራቅ አከጃ ከተማ በነጻ የምግብ ዕደላ ላይ በተከሰተ ግፊያና መረጋገጥ የሟቾች ቁጥር 22 ደረሰ። ነጻ ምግብ በሚታደልበት ወቅት ሰዎች ተረጋግጠው ሲሞቱ ይህ በዚህ ሳምንት ለሶስተኛ ጊዜ እንደሆነ ተገልጿል።

የጎሮጎሮሳውያኑን የዘመን አቆጣጠር በሚከተሉት ዘንድ የሚከበረውን የገና በዓል አስመልክቶ ቅዳሜ ዕለት እየተደረገ በነበረ ርዳታ ላይ ነው ይህ ግርግር የተፈጠረው። በርካቶች ሩዝ እና ዘይት ለመውሰድ በሚጣደፉበት ወቅት በተነሳው መረጋገጥ ሰዎች ተጨፍልቀው መሞታቸው ተገልጿል።

በተመሳሳይ ዕለት በዋናዋ ከተማ አቡጃ በሚገኘው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተመሳሳይ አደጋ ተከስቶ አስር ሰዎች ሞተዋል። ከዚያ ቀደም ብሎ ባለፈው ሳምንት ረቡዕ ዕለት ኢባዳን በተሰኘችው ከተማ በነበረ የካርኒቫል ዝግጅት የ35 ህጻናት ሕይወት ተቀጥፏል።

ፖሊስ እንደዚህ አይነት የሕይወት መጥፋትን ለመከላከል ዕርዳታ ሰጪዎች የበጎ አድራጎት ዝግጅቶችን ከማድረጋቸው በፊት ለባለሥልጣኑ እንዲያሳውቁ አስጠንቅቋል።

በአቡጃ የቅድስት ሥላሴ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በነበረው ዕርዳታ አሰጣጥ ላይ በርካቶች የቤተ ክርስቲያኑን በር ጥሰው እንደገቡ ቶይን አብዱል ካድሪ የተሰኙ የዓይን እማኝ ተናግረዋል።

በዚህም አዛውንቶች ጭምር የተጎዱ ሲሆን አራት ህጻናት መገደላቸውን ፖሊስ ተናግሯል። በናይጄሪያ የምግብ እና የትራንስፖርት ወጪዎች ባለፉት 18 ወራት ብቻ ከሶስት እጥፍ በላይ ጨምሯል። የዓለም አቀፍ የዋጋ ግሽበት እና መንግሥት እየተከተላቸው ያሉ እንደ ነዳጅ ድጎማ ማቆም የኑሮ ውድነቱን የበለጠ የከፋ አድርገውታል።

"በደስታ እና በበዓል ሰሞን ዜጎቻችን በወገኖቻቸው ላይ በደረሰው አሰቃቂ መታጣት አብረናቸው እናዝናለን። መጽናናትን እንዲያገኙ ጸሎታችን ከእነሱ ጋር ነው" ሲሉ ነው ፕሬዚዳንት ቦላ ቲኑቡ የገለጹት። የክልል መንግሥታት እና ፖሊስ ሕዝብ በሚሰባሰብባቸው ሥፍራዎች ጥብቅ የሆኑ የቁጥጥር ርምጃዎችን እንዲተገብሩ አሳስበዋል። ሕይወታቸውን ላጡ ተጎጂዎችን ለማሰብ መንግሥታቸው አቅዶ የነበሩ ዝግጅቶች እንዲሰረዙ ትዕዛዝ ሰጥተዋል።

በተጨማሪም በባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ላይ በኢባዳን ከተማ የተከሰተውን ግርግር ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ጠቅሰዋል። በአንድ ትምህርት ቤት በነበረ የካርኒቫል ዝግጅት ላይ ነጻ ምግብ እንደሚታደል መነገሩን ተከትሎ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች መምጣታቸውን ተከትሎ 35 ህጻናት ተገድለዋል። እንዲሁም ስድስት ሰዎች መጎዳታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ቻይና ‘‘አሜሪካ በእሳት እየተጫወተች ነው’’ ስትል አስጠነቀቀች

አሜሪካ በታይዋን አካባቢ የምታደርገውን አደገኛ እንቅስቃሴ እንድታቆም ቻይና አሳሰበች። የተሰናባቹ የባይደን አስተዳደር ለታይዋን የ571 ሚሊዮን ዶላር ወታደራዊ ድጋፍ ፈቅዷል፡፡

አሜሪካ ለታይዋን ተጨማሪ የወታደራዊ ድጋፍ እና ሽያጭ ይፋ ማድረጓን ተከትሎ ቤጂንግ ዋሽንግተንን በእሳት እየተጫወተች ነው ስትል አስጠንቅቃለች።

የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ፤ አሜሪካ በታይዋን ሰርጥ ውስጥ የምታካሂደውን ሰላምና መረጋጋትን የሚጎዱ አደገኛ እንቅቃሴዎች እንድታቆም አሳስቧል።

የዋይት ሃውስ ባሳለፍነው አርብ ባወጣው መግለጫው የተሰናባቹ የፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አስተዳደር ለታይዋን የ571 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዶላር ወታደራዊ ድጋፍ መፍቀዱን አስታውቋል።

የዋይት ሃውስ መግለጫ ስለ ወታደራዊ ድጋፉ ዝርዝር ጉዳዮችን ባይሰጥም፣ አሜሪካ ለታይዋን ወታደራዊ ድጋፍ ስትፈቅድ ከሶስት ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ እንደሆነ ተገልጿል።

የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር “ይህ ርምጃ የቻይናን ሉዓላዊነት እና የደህንነት ጥቅሞችን በእጅጉ ይጥሳል” ያለ ሲሆን እንዲህ አይነቱን ተግባር በጽኑ እንደሚቃወምም አስታውቋል።



የቻይና የታይዋን ጉዳይ ፅህፈት ቤት በጉዳዩ ላይ በሰጠው መግለጫ፤ አሜሪካ የጦር መሣሪያ ድጋፍ ርምጃ መሪዎቿ የታይዋንን ነጻ ሀገርነት አንደግፍም የሚለውን አቋም የሚቃረን ነው ብለዋል።

አሜሪካ ለታይዋን የምታደርገውን የመሣሪያ ድጋፍ በአስቸኳይ እንድታቋምና የታይዋንን ጉዳይ በከፍተኛ ጥንቃቄ እንትይዘው የጽህፈት ቤቱ ቃል አቀባይ ዝሁ ፍሪንግሊያን አስታውቀዋል።

ቤጂንግ የሉዓላዊ ግዛቴ አካል ናት የምትላትን ታይዋን እንደ ሉዓላዊ ሀገር ከሌሎች ሀገራት ጋር መሰል ስምምነት መፈራረም እንደማትችል ደጋግማ ማሳሰቧ ይታወሳል።

ታይዋን ግን ባለፉት ሶስት ዓመታት በተለይ ከአሜሪካ ጋር ወዳጅነቷን አጥብቃ የጦር መሣሪያ ሽያጭ ስምምነቶችንም ፈጽማለች።

ይህ በጦር መሣሪያ ሽያጭ የሚታይ የዋሽንግተን ጣልቃገብነት የቤጂንግን ወታደራዊ ዝግጁነት እያጠናከረው ስለመምጣቱም ነው የሚነገረው።

በየእለቱም በታይዋን ሰርጥ አካባቢ ቅኝት የሚያደርጉ የቻይና አውሮፕላኖች ቁጥር እየጨመረ መሄዱም ውጥረቱን አንሮታል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።

# ስፖርት





# ከአዳዲሶቹ የአትሌቲክስ አመራሮች አንደበት

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ከትናንት በስቲያ ፌዴሬሽኑ ባደረገው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ አዳዲስ መሪዎችን አግኝቷል። የቀድሞው ስኬታማ የረጅም ርቀት ኮከብ አትሌት ኮማንደር ስለሺ ስህን ለቀጣዩ አራት ዓመት ፌዴሬሽኑን በፕሬዚዳንትነት እንዲያገለግል መመረጡ ይታወቃል። በተመሳሳይ ለስፖርቱ ቅርብ የሆኑ ግለሰቦችና የቀድሞ ኮከብ አትሌቶችም ለፌዴሬሽኑ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት መመረጥ ችለዋል፡፡

ይህንን ተከትሎም ባለፉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት በአስተዳደራዊ ችግሮች እያሽቆለቆለ የመጣው የአትሌቲክስ ውጤት አንድ መፍትሄ ያገኛል የሚል ተስፋ በብዙዎች ዘንድ አድሯል፡፡ ጠቅላላ ጉባዔውም ለአዲሱ አመራር የኢትዮጵያ መለያ የሆነውን የአትሌቲክስ ውጤት እንዲስተካከልና ባለፉት ዓመታት ሕዝብ ያሳዘኑ አስተዳደራዊ ችግሮች እንዲስተካከሉ ሃላፊነት ሰጥቷል፡፡

ፕሬዚዳንታዊ ምርጫው ከ26 ድምጽ 11 በማግኘት ያሸነፈው የቀድሞው አትሌት ኮማንደር ስለሺ የኢትዮጵያ ኩራት የሆነውን ስፖርት ለማገልገል በመመረጡ ምስጋናውን አቅርቧል፡፡ ጠንካራ ፉክክር በተደረገበት ምርጫ ላይ የፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሆነው የተመረጡትም አትሌቶች፣ ምሁራንና ባለሀብቶች እንደመሆናቸው ለአንድ ዓለማ እንደሚሠሩ ቃል ገብተዋል፡፡ በረጅም ርቀት የተወዳዳሪነት ዘመኑ በርካታ የብር ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ የሚታወቀው ስለሺ ስህን «siliver man» በሚል ቅጽል ስም ይታወቃል፡ ፡ የቀድሞው የኢትዮጵያ አትሌቶች ማህበር ፕሬዚዳንት አሁን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን ቁንጮ ሆኖ ለመምራት ሲመረጥ ሥራውን ከአዳዲሶቹ የሥራ አስፈጻሚ አባላት ጋር በመነጋገርና ለምርጫው ይዘው



**አዲሱ የአትሌቲክስ አመራር ስፖርቱን ካለበት ችግር ለማውጣት በጋራ እንደሚሠራ ቃል ገብቷል፣**

የቀረቧቸውን እቅዶች አዳብረው የጋራ በማድረግ እንደሚጀምር ተናግሯል፡፡ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ትልቅ ፌዴሬሽን እንደመሆኑ የሚያሳስቡ ነገሮች ይኖራሉ የሚል ስጋቱን የገለፀው ስለሺ፣ በተቻለው መጠን አትሌቶችን፣ አሠልጣኞችን፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማስደሰት ከተመረጡት ሥራ አስፈፃሚዎች ጋር በመሆን ኢትዮጵያን የሚመጥን ነገር ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ተናግሯል፡፡ «አጠቃላይ ለምርጫው ተወዳዳሪ የሆኑ የስፖርቱ ቅርብ ሰዎች በዚህ ደረጃ ቀርበው ለማገልገል መምጣታቸው ትልቅ ነገር ነው፤ እንግዲህ ምርጫ ነው እኔ አልፌያለሁ እነሱ ቀርተዋል፤ በሌላ ጊዜ ይመጣሉ፣ ያገለግላሉ ብዬ አስባለሁ፤ ነፃ አገልግሎት ነው፤ ባይገቡም ደግሞ ያግዙናል ብዬ አስባለሁ» ሲልም ስለተፎካካሪዎቹ አስተያየት ሰጥቷል፡፡

በቀጣይ አራት ዓመታት የአትሌቱን፣ የአሠልጣኞችን፣ የስፖርት ቤተሠቡን ዕንባ ለማበስ ቁርጠኛ መሆኑን በተመለከተ በሰጠው አስተያየትም «መቶ በመቶ እንባ ለማበስ ነው የምመጣው፤ ለእኔ ዕውነት፣ ዕውነት ነው፤ በዛ ላይ ቤቱን አውቀዋለሁ ማንንም ለመጥቀም፣ ማንንም ለመጉዳት አንሄድም፣ አልሄድምም፣ አድርጌም አላውቅም፤ ሳናውቅ ሠው ልናስቀይም እንችላለን፤ ግን አውቀን አናደርግም፣ የተለየ ፍላጎትም የለንም፤ ፍላጎታችን ስፖርትና ስፖርት ብቻ ነው፣ አንድ ሀገር፣አንድ ዓላማ ነው ያለን ለሀገራችን የሚጠቅመውን ነገር እናደርጋለን ብዬ አስባለሁ» በማለት ተናግሯል፡፡

በዓለም ቻምፒዮና እና በኦሊምፒክ መድረኮች ውጤታማ የሆነችው አትሌት መሠረት ደፋርም በጉባዔው የተመረጠች የሥራ አስፈጻሚ አባል ናት፡፡ ከዚህ ቀደም የአትሌት ተወካይ በመሆን የሠራችው መሠረት በተለይ እንደ አዲስ አበባ ባሉና ሴት ታዳጊ አትሌቶች ውጤታማ ባልሆኑባቸው ከተሞች እንዲሁም ውድድሮች ላይ ትኩረት አድርጋ ለመሥራት ማቀዷን ጠቁማለች፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በመሆን ያገለገለው የማርሽ ቀያሪው ምሩፅ ይፍጠር ልጅ ቢንያም ምሩጽም በሥራ አስፈጻሚነት መካተት ችሏል፡፡ ቢኒያም በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ከአባላቱ ጋር እንደሚሠራ ይናገራል፡፡ በተለይ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችና ከፊት ለሚካሄደው ዓለም ቻምፒዮና የአትሌቶች መምረጫ መስፈርቶችን ማዘጋጀት እንዲሁም በ2017 ዓም ዕቅዶችን በመመልከትና በመከለስ ስኬታማ ተግባር ለማከናወን ዝግጁ መሆኑንም አረጋግጧል፡፡

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ከተቀላቀሉት መካከል አንዱ የኢትዮ ኤሌክትሪክ አትሌቲክስ ክለብ አመራር የሆኑት ኢንጂነር ጌቱ ገረመው በበኩላቸው፣ ሥራ አስፈጻሚው በጋራ በማቀድና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አትሌቲክሱን የሚመጥን ሥራ ማከናወንና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡ በተለይ የፌዴሬሽኑ ሪፎርም፣ የአትሌቶችን ችግር የመፍታት፣ በተለያዩ ምክንያት ተቃርኖ ከተፈጠረባቸው አካላት ጋር እርቅ መፈጸም ቀዳሚዎቹ ሥራዎች እንደሚሆኑ አስረድተዋል።

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት ሚኒስትር ዴኤታ መኪዩ መሀመድ በጠቅላላ ጉባዔው ተገኝተው በሰጡት አስተያየት፣ አትሌቲክስ ለኢትዮጵያውያን ስፖርት ብቻ ሳይሆን ማንነትም ጭምር መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ ብርቅየ አትሌቶች ብዙ ታሪክ ባኖሩበት የኦሊምፒክ መድረኮች ሁሉ ነገር በተመቻቸበትና መንግሥትም ለዘርፉ ትኩረት በሰጠበት በዚህ ዘመን ለምን ወደኋላ ተመለስን የሚለው ጉዳይ አዲሱን የአትሌቲክስ አመራር ሊያስቆጭ ይገባልም ብለዋል፡፡ አዲሱ አመራር ስፖርቱ ካለበት ብልሹ አሠራር በማውጣትና ወደ ገናና ስሙ በመመለስ ሕዝቡን ለመካስ በቅንነትና በታማኝነት ሊያገለግል እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡